ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 325 ሐምሌ 25 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ መግባት ምን ፋይዳ ይኖረው ይሆን?

**ዜና ትንታኔ**

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

በኢትዮጵያ ለረጅም ዓመታት በቁጥር ውስን የነበሩ ባንኮች በአሁኑ ጊዜ ከ30 በላይ ደርሰዋል፡፡ ከሰሞኑ መንግሥት የፋይናንስ ሥርዓቱን ለማዘመን ብሎም ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትን ለማረጋገጥ ይበጃሉ ያላቸውን የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተከትሎ በቀጣይ የውጭ ባንኮች ወደ ሀገራችን ይገባሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ለመሆኑ የባንኮቹ ወደ ሀገር መግባት ለሀገር ኢኮኖሚ ምን ያስገኛል? ተግዳሮቶችስ ምን ሊሆኑ ይችላሉ? ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ከማሳደግ አኳያ ምን ሚና ይኖራቸዋል? በሚሉት ነጥቦች ዙሪያ ምሁራን ሃሳባቸውን ሰጥተውናል፡፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ክቡር ገና እንዳሉት፣ የውጭ ባንኮች ወደ ሌሎች ሀገራት የሚሄዱት ሰርቶ ለማትረፍ ነው፡፡ የባንኮቹ ዓላማ የተሻለ አገልግሎት ሰጥቶ ደንበኞችን መያዝና ትርፍ ማግኘት መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

ልክ እንደ ሀገር ውስጥ ባንኮች ዋጋ ከፍለው እስከ ሀገራችን ጥግ ድረስ ሄደው አገልግሎት የመስጠት ፍላጎትም አይኖራቸውም፡፡ ባንኮቹ ዶላር ይዘው ለመሄድ እንጂ ዋጋ ከፍለው ለማገልገል አይመጡም ይላሉ፡፡

እርሳቸው እንዳሉት፤ ባንኮቹ ዶላር ይዘው ለመሄድ እንጂ ብር ይዘው ወደ ሀገራቸው ለመሄድ አይመጡም፤ ቢሆንም ግን፣ በባንኩ ዘርፍ ያለውን ተወዳዳሪነትን ከፍ በማድረግ ረገድ ጠቀሜታ እንደሚኖራቸው ይናገራሉ፡፡

**የውጭ ባንኮች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**




# አደጋን የመከላከል አቅም የመገንባት ጥረት

**ዘሳስም ግዛው**

በጎፋ ዞን ኬንቾ ሻቻ ጎዝዲ ቀበሌ ሰሞኑን በደረሰው የመሬት መንሸራተት አደጋ ይህ መረጃ እስከተጠናከረበት ጊዜ ድረስ የሟቾች ቁጥር 226 ደርሷል፡፡ አሰቃቂውን አደጋ ተከትሎ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሐምሌ 20 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ለሦስት ቀናት የቆየ ብሔራዊ ኀዘን ማወጁም ይታወሳል፡፡

ከሰኔ እስከ መስከረም ወራት ድረስ እጅግ በጣም የከፋ ጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተትና የውሃ ሙላትን ሊያስከትል የሚችል ዝናብ

**አደጋን የመከላከል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

# 78 ዓመታትን በስኬት የዘለቀው ተቋም

**ዜና ትንታኔ**

**ሄለን ወንድምነው**

ተቋሙ ለኢትዮጵያ ገጽታ ግንባታና ኢኮኖሚያዊ እድገት ጉልህ አስተዋጽኦን አበርክቷል:: ኢትዮጵያ ከሌሎች ዓለም ሀገራት ጋር በንግድ፣ በቱሪዝም፣ በኢንቨስትመንትና በሌሎች ዘርፎች መልካም ግንኙነት እንዲኖራት አድርጓል:: የ 78 ዓመት የእድሜ ባለጸጋው አንጋፋ ተቋም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ::

**78 ዓመታትን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**








ፎቶ አዮብ ተፈራ

አቶ ባዩህ አቡሀይ

# በጎንደር ከተማ ለ105 አልሚ ባለሀብቶች መሬት ተሰጥቷል

**ሄለን ወንድምነው**

ጎንደር፡- በ2016 በጀት ዓመት ለ105 አልሚ ባለሀብቶች 92 ነጥብ አምስት ሄክታር መሬት ማስተላለፉ የከተማዋ ከንቲባ አቶ ባዩህ አቡሀይ ገለጹ።

የጎንደር ከተማ ከንቲባ አቶ ባዩህ አቡሀይ እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት ጎንደርን የኢንቨስትመንት ተመራጭ ከተማ በማድረግ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ሲሠራ ቆይቷል። በ2016 በጀት ዓመት ለ105 አልሚ ባለሀብቶች 92 ነጥብ አምስት ሄክታር መሬት ተሠጥቷል።

ባለፈው በጀት ዓመት 116 ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ 349 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ በመስጠት 92 ነጥብ አምስት ሄክታር መሬት ለ105 ባለሀብቶች ማስተላለፍ መቻሉን ገልጸዋል።

በጎንደር ከተማ ያለው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪ መሆኑን ገልጸው፤ በተያዘው ዓመት ብቻ 27 ፕሮጀክቶችን ወደ ምርት ለማስገባት ታቅዶ 23ቱ ምርት ማምረት ጀምረዋል። ሰባት ፕሮጀክቶች ደግሞ ማሽን ተከላ ላይ መሆናቸውን አመላክተዋል።

ኢንዱስትሪዎች እንደ ሀገር የሚገጥመውን የውጭ ምንዛሬ እጥረትን እንዲፈቱና ምርትን በሀገር ውስጥ እንዲተኩ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው ያሉት ከንቲባው፤ በዚህ ዓመት ስምንት ኢንዱስትሪዎች 18 ሺህ 328 ቶን ምርትን ወደ ውጭ ሀገር በመላክ 49 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ዶላር ገቢ አስገኝተዋል ብለዋል።

ባለፉት ዓመታት በክልሉና በከተማው አቅም አምስት የኢንዱስትሪ መንደሮችን መከለል እንደተቻለ ገልጸው፤ አራቱ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ መሠረተ ልማት ተሟልቶላቸው ለባለሀብቶች ተላልፈዋል። ኢንዱስትሪ መንደር ቁጥር አምስት ደግሞ ለባለሀብቱ ካሳ እየተላለፈ ይገኛል ነው ያሉት።

በአምስቱም የኢንዱስትሪ መንደሮች 46 በቅድመ ግንባታ፣ 137 በግንባታ ላይ ፣ ግንባታ ያጠናቀቁ 70፣ በምርት ላይ ያሉ 192 በአጠቃላይ 445 ፕሮጀክቶች መኖራቸውን አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ባዩህ ገለጻ፣ ኢንዱስትሪዎች ሲስፋፉ የከተማውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ከማሳላጥ ባለፈ የውጭ ምንዛሬን ለማስገኘት፣ ተኪ ምርትን ለማምረትና የሥራ እድል ለመፈጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ።

ባለፈው በጀት ዓመት ወደ ሥራ እየገቡ ባሉ ኢንዱስትሪዎች ብቻ ለአምስት ሺህ 71 ወጣቶች የሥራ እድል ተፈጥሯል ሲሉ ተናግረዋል።

አካባቢው የቅባት እህሎች፣ ቅመማቅመምና ሌሎች ሰብሎች የሚመረትበት በመሆኑ ለአግሮ ፕሮሰሲንግና ለሌሎች ዘርፎች ምቹ መሆኑን ገልጸው፤ እስካሁን የተሰሩት ሥራዎች ከተማው ከሚፈልገውና ካለው የልማት እድል አንጻር በቂ ባይሆንም በጸጥታ ችግር ውስጥ ሆኖ የተሠሩት ሥራዎች ተስፋን የሚሰንቁ ናቸው ብለዋል።

# በሌማት ቱርፋት ከሌማታቸው የተሻገሩ ብርቱዎች

**ፋንታነሽ ክንዴ**







የሌማት ቱርፋት ንቅናቄ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጪነት ወደ ሥራ ከገባ በኋላ ብዙዎችን የሀብት ባለቤት አድርጓል። ትኩረት ተነፍጓቸው የቆዩ የየአካባቢው ጸጋዎች እንዲታዩና አዲስ የሥራ ባህል እንዲፈጠርም አስችሏል። ሥራ ፈላጊዎች ሥራ ፈጣሪ፤ ከእጅ ወደ አፍ ሲኖሩ የነበሩትም ትርፍ አምራች ሆነዋል። በዚህም የጎደለ ሌማታቸውን ከመሙላት አልፈውም ለገበያ በማቅረብ የሌሎችን ጫና እያቀለሉ ይገኛሉ።

ማዕከላዊ ኢትዮጵያ በሌማት ቱርፋት ጥሩ ውጤት ከተመዘገበባቸው ክልሎች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው። ወጣቶች፣ አርሶ አደሮችና የመንግሥት ሠራተኞችም ሳይቀር በሥራው ላይ እየተሳተፉ ይገኛሉ።

ወጣት አቤል ሙሉጌታ በምሥራቅ ጉራጌ ዞን የቡታጅራ ከተማ ነዋሪ ነው። ከተማ አስተዳደሩ ባመቻቸላቸው ቦታ ከአራት ጓደኞቹ ጋር በመሆን ቀሽት የንብ ማነብ ማህበርን መሥርተው ወደ ሥራ ገብተዋል። እሱም ማህበሩን በሥራ አስኪያጅነት ይመራል።

በ2015 ዓ.ም ከእያንዳንቸው ኪስ በተዋጣ 110 ሺህ ብር 20 ቀፎዎችን በመግዛት ሥራውን እንደጀመሩ የሚያስታውሰው ወጣት አቤል፤ አሁን ላይ ሥራው ሰፍቶ የ450 ዘመናዊና የ300 ባህላዊ ቀፎዎች ባለቤት መሆን ችለዋል። ከማር ባለፈ ሰም እንዲሁም ሕብረ ንብ እያባዙ ለገበያ ያቀርባሉ።

አካባቢው ለማር ምርት ምቹ በመሆኑ ከአንድ ቀፎ በዓመት በአማካይ ከ50 ኪሎ ግራም በላይ ምርት እናገኛለን፤ ይህም ሕይወታችን ላይ ትልቅ ለውጥ አምጥቶልናል ይላል።

ለውጤታማነታቸው የሥራ ቦታ ማመቻቸትን ጨምሮ በየደረጃው ባሉ የመንግሥት አካላት የተደረገላቸው ድጋፍ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው የሚጠቅሰው ሥራ አስኪያጁ፤ ሌሎች ወጣቶች የእነሱን ፈለግ ተከትለው ወደ ሥራ እንዲገቡና ሕይወታቸውን እንዲለውጡ ልምዳቸውን እንደሚያካፍሉ፤ ሥልጠናን ጨምሮ ሌሎችንም አስፈላጊ ቁሳቁሶች ድጋፍ እንደሚያደርጉም ይገልጻል።

ባለፉት ዓመታት ያካበቱትን ልምድ ተጠቅመው ሥራቸውን ወደ 20 ሺህ ቀፎ በማድረስ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተጠቃሽ የሆነ ግዙፍ የንብ ማነቢያ ማዕከል መገንባትን ራዕይ አድርገው እንደሚሠሩ የሚጠቁመው ወጣቱ፤ ምርቱ ላይ እሴት ጨምረው ወደ ውጭ ለመላክም እቅድ አላቸው።

እቅዳችንን ከዳር ለማድረስ ጥረት እናደርጋለን፤ መንግሥትም እስካሁን ሲያደርግልን የነበረውን ድጋፍ አጠናክሮ ይቀጥል ሲል መልዕክቱን ያስተላልፋል።

አርሶ አደር በላይነህ መንቴ በከምባታ ዞን ቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ የዛቶ ሾደራ ቀበሌ ነዋሪ ናቸው። በሚያከናውኑት የጥምር ግብርና ሥራ አስር ቤተሰባቸውን ያስተዳድራሉ። በሌማት ቱርፋት ንቅናቄ በተፈጠረላቸው ግንዛቤ ውጤታማ ያልነበሩ የላም ዝርያዎችን ወደ ተሻሻሉ ዝርያዎች በመለወጥ በወተት ልማት ውጤታማ መሆን ችለዋል።

ላሞቹ ከወለዱበት ጊዜ ጀምሮ አራት ወራት ድረስ በቀን ሦስት ጊዜ ወተት ይሰጣሉ የሚሉት አርሶ አደሩ፤ ከአራት ወር በኋላም በቀን ሁለት ጊዜ ይታለባሉ።

ጠዋትና ቀን የሚታለበው ወተት ለገበያ የሚቀርብ ሲሆን፣ የማታው ደግሞ ለቤተሰቡ ፍጆታ ይውላል። ይህም ለቤተሰቡ የተመጣጠነ ምግብ ማቅረብ፣ ለገበያ ከሚቀርበውም ተጨማሪ ገቢ ማግኘት አስችሏቸዋል።

ባለሙያዎች በሚያደርጉላቸው ድጋፍ የላሞችን ጤንነት በመጠበቅና አመጋገባቸውን በማስተካከል ምርታማነታቸውን ለማሳደግ እንደሚሰሩ የሚገልጹት አርሶ አደሩ፤ በቀጣይነትም ሥራውን አስፍተው ወደ እንስሳት እርባታ ማዕከል የማሳደግ እቅድ ይዘዋል። የሌማት ቱርፋት ንቅናቄ አካባቢያችንን ጸጋ እንድናውቅና እንድንጠቀም በማድረግ የብዙ ሰዎችን ሕይወት እየቀየረ ነው ይላሉ።

ከከፍተኛ አመራሩ ጀምሮ በየደረጃው ያለው አመራር ለሚያደርጉት ጠንካራ ድጋፍና ክትትልም ምስጋና አቅርበዋል።

አቶ ተመስገን ሶደኖ እና ወይዘሮ የተመኝ አሰፋ በሀላባ ዞን የሀላባ ቁሊቶ ከተማ ነዋሪ ጥንዶች ናቸው። አቶ ተመስገን የዞኑ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ባልደረባ ሲሆኑ፤ ባለቤታቸው ደግሞ በሀላባ ቁሊቶ ከተማ ውሃ አገልግሎት ውስጥ ይሠራሉ።

እንደሀገር የተፈጠረው የኑሮ ውድነት ቤታቸውን ሲያንኳኳ እንደነበር የሚያስታውሱት ጥንዶቹ፤ በተለይ ለልጆች ምግብ በዋና ግብዓትነት የሚጠቀሙት እንቁላል 15 ብር መግባት አሳስቧቸው ነበር። በዚህም ምክንያት እንደማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ችግሩ እንዲቀረፍ ደጋግመው ሲጠይቁ ቆይተዋል።

የሌማት ቱርፋት ንቅናቄ ዞኑ ላይ ተግባራዊ ሲደረግ ግን ከጠያቂነት ይልቅ የመፍትሔው አካል መሆን ፈልጉና በጓሯቸው ዘመናዊ የዶሮ ርባታ ጀመሩ። አሁን ላይ አርባ ዶሮዎችን እያረቡ ሲሆን፤ በየቀኑ ከ37 ያላነሰ እንቁላል ያገኛሉ። ይህም የቤተሰቡን ፍላጎት ከማሟላት አልፎ ለገበያ ማቅረብ አስችሏቸዋል።

የዶሮ ልማት ጥቂት ቦታ ላይ መሠራት የሚችልና ብዙም ጊዜ የማይፈልግ ነው የሚሉት ጥንዶቹ፤ ጠዋት ላይ ማደሪያቸውን አጽድተውና ምግባቸውን አቅርበው ይሄዳሉ። ለምሳ ወደ ቤት ሲመለሱም ቅድሚያ ዶሮዎችን የመንከባከብና የጣሉትን እንቁላል የማንሣት ሥራን ይሠራሉ። በየጊዜው ክትባት እንዲያገኙና ተገቢው የባለሙያ ክትትል እንዲኖራቸውም ይሠራሉ።

የሌማት ቱርፋት ንቅናቄ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ ብዙዎችን ባለሀብት እያደረገ መሆኑን የሚያስታውሱት እነዚህ ብርቱ ጥንዶች፤ ገበያውን በማረጋጋት በኩልም ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

በቀጣይነት ሥራቸውን አስፍተው የመሥራት እቅድ እንዳላቸው የሚገልጹት ጥንዶቹ፤ አካባቢያቸው ላይ እምቅ ሀብት እያለ ሥራ የለም በሚል የተሳሳተ ግንዛቤ ጊዜያቸውን በከንቱ የሚያሳልፉ ወጣቶች መኖር የለባቸውም። ሁሉም አካባቢውን መመልከትና ዝቅ ብሎ ሠርቶ ቀና ብሎ ለመሄድ ቁርጠኛ መሆን አለበት ሲሉም መልእክታቸውን ያስተላልፋሉ።

# በዞኑ በዘንድሮ ዓመት ከ278 ሚሊዮን በላይ ችግኞች ይተከላሉ

## - ከመኸር እርሻ 19 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን በዘንድሮ ዓመት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር ከ278 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን ዞኑ ገለጸ። ከመኸር እርሻ 19 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት እየተሠራ እንደሚገኝም ተጠቁሟል።

የምስራቅ ሸዋ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አባቡ ዋቆ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተካሄደ የሚገኘውን የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር መነሻ በማድረግ በዞኑ በሚገኙ 11 ወረዳዎች ውስጥ ከ278 ሚሊዮን በላይ ችግኞች ለመትከል ታቅዶ እየተሠራ ነው።

ከሚተከሉት ችግኞች ውስጥ 35 በመቶ የሚሆኑት ለምግብነት የሚያገለግሉ የአቮካዶ፣ ሙዝ፣ ፓፓዬ፣ ብርቱካን፣ ቴምርና ሌሎችም እንደሆኑ አብራርተዋል።

በፍራፍሬ ዛፎች ላይ ትኩረት መደረጉን ያነሱት ዋና አስተዳዳሪው፤ የተቀረው ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለውበትና ለከብቶች መኖ የሚያገለግል መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ አስተዳዳሪው ገለጻ፤ ዞኑ ለአቮካዶ ምርት ተስማሚ የአየር ሁኔታ ያለው በመሆኑ ከአረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር ጋር በማያያዝ በስፋት እየተሠራበት ይገኛል።

ዞኑ የአቮካዶ ምርትን ለአውሮፓ ገበያ ለማቅረብ ጥረት እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ዘንድሮ ለሶስተኛ ጊዜ ዘጠኝ ሺህ ኩንታል አቮካዶ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ተችሏል ብለዋል።



አቶ አባቡ ዋቆ

ምርታማነቱን ለማሳደግ አምና 900 ሄክታር መሬት ብቻ ለአቮካዶ ምርት አምራቾች ይሰጥ የነበረ መሆኑን አንስተው፤ በዘንድሮው ዓመት ወደ አንድ ሺህ 200 ሄክታር ከፍ ማድረግ መቻሉን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ አቮካዶ ምርት በሚደርስበት ወቅት የሌሎች አምራች ሀገራት ምርት ወደ ገበያ የሚወጣበት ወቅት ባለመሆኑ ይህንን እንደምቹ አጋጣሚ በመጠቀም ገበያውን የማሳደግ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በሁሉም ወረዳዎች በሚገኙ ችግኝ ጣቢያዎች ላይ እራሱን የቻለ የአቮካዶ ችግኝ ማፍያ ሼድ ተዘጋጅቶ የምርት አሰጣጥ ሁኔታው በጥናት የተረጋገጠለት ሀስ የሚባል ዝሪያ እየተዘጋጀ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በዚህ ረገድም ለበርካታ ሥራ አጥ ወጣቶች የሥራ እድል መፍጠር ከመቻል ባሻገር አርሶ አደሩም በቅርበት ችግኝ እንዲያገኝ እየተደረገ ነው ብለዋል።

በዞኑ በመኸር እርሻ 583 ሺህ ሄክታር መሬት በማልማት 19 ሚሊዮን ኩንታል ለማግኘት እየተሠራ መሆኑን ያነሱት አስተዳዳሪው አያይዘው ገልጸዋል።

ከዚህ ውስጥ ከ240 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በስንዴ እንደሚለማና በተጨማሪም ሩዝ፣ ቦሎቄ፣ አኩሪ አተር፣ በቆሎና ጤፍ ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

በአሁኑ ወቅት በስንዴ ልማት በተሰራው ከፍተኛ ሥራ 400 ሺህ ሄክታር መሬት በመስኖ በማልማት እስከ 16 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት እየተገኘ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከማዳበሪያና የምርጥ ዘር አቅርቦት ጋር በተያያዘ በተከናወኑ በርካታ ተግባራት ከአምና የተሻለ ማድረግ መቻሉን የጠቆሙት አስተዳዳሪው፤ ከሁለት ዓመት በፊት አርሶ አደሮች 530 ሺህ ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ይጠቀሙ እንደነበርና ፍላጎቱ እየጨመረ በመምጣቱ ዘንድሮ ለአርሶ አደሩ ብቻ 720 ሺህ ኩንታል ማዳረስ መቻሉን ተናግረዋል።

እንደ አቶ አባቡ ገለጻ፤ ከምርጥ ዘር ጋር በተያያዘ የስንዴ፣ የሩዝና የጤፍ ምርቶች ምርጥ ዘር በፍላጎቱ ልክ ማቅረብ ተችሏል። በሌሎች በተወሰኑ ሰብሎች ላይ ፍላጎቱ ከፍተኛ በመሆኑ ማሟላት አልተቻለም። ነገር ግን ችግሩን ለመፍታት የሰብል ዘርን በዩኒየኖችና ከተለያዩ ማህበራት ጋር በመሆን የማባዛት ተግባር እየተከናወነ ነው።



# ብድሩ የሪፎርም ሥራዎችን ለመደገፍ እንደሚውል ተገለጸ

**ተስፋ ፈሩ**

አዲስ አበባ፡- ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር በብድር የተገኘው 500 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሪፎርም ሥራዎችን ለመደገፍ እንደሚውል በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ተስፋዬ በልጅጌ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው 3ኛ አመት የስራ ዘመን 1ኛ አስቸኳይ ስብሰባ በኢትዮጵያ እና በዓለም አቀፉ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት አዋጅ አጽድቋል፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ተስፋዬ በልጅጌ (ዶ/ር) ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር በብድር የተገኘው 500 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የኢትዮጵያ መንግሥት የጀመራቸውን የሪፎርም ሥራዎች ለመደገፍ እንዲሁም የፌዴራል መንግሥትን የ2017 በጀት በቀጥታ ለመደገፍ እንደሚውል ገልጸዋል።

ተጠሪ ሚኒስትሩ የብድር ሥምምነት ረቂቅ አዋጁን አስመልክቶ በሰጡት ማብራሪያ፤ ከለውጡ በኋላ ገቢራዊ የሆነው የመጀመሪያው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ብዙ ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎችን ተቋቁሞ መልካም ውጤት ማስመዝገብ መቻሉን ጠቅሰዋል።

ባለፉት የለውጥ ዓመታትም በአማካይ 6 ነጥብ 2 በመቶ እድገት ማስመዝገብ የተቻለበት መሆኑንም ጠቁመው፣ በሁለተኛው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም እንቅስቃሴ የማክሮ ስብራቶችን ለመጠገን እንዲሁም በመጀመሪያው ምዕራፍ የተገኘውን ውጤት ለማስቀጠል በትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በዚህም መሠረት የማክሮ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት በተለይም ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስና ለመቆጣጠር፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅረፍና የመዋቅር ማስተካከያ ለማምጣት የሚያስችሉ የሪፎርም ሥራዎች ወደ ሥራ መግባታቸውን አመላክተዋል።

ዓለም አቀፉ የልማት ማኅበር መልካም ውጤት ያስመዘገበውን ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ-ግብር ለመደገፍ፣ ለመጀመሪያው ዘላቂና ሁሉን አቀፍ የእድገት ልማት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የሚውል አንድ ቢሊዮን ዶላር ርዳታና 500 ሚሊዮን ዶላር ብድር ለኢትዮጵያ መንግሥት ለመስጠት በመስማማቱ ከማኅበሩ ጋር የገንዘብ ድጋፍና የብድር ሥምምነት መፈረሙን የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

500 ሚሊዮን ዶላር ብድሩ ከወለድ ነፃ፤ ባንኩ በሚወስነው መሠረት ጥቅም ላይ ባልዋለው የብድር ገንዘብ ላይ በዓመት እስከ 0 ነጥብ 5 በመቶ የሚደርስ የግዴታ ክፍያ ሊከፈልበት የሚችል፤ ባንኩ የብድሩን ገንዘብ በማስተዳደር ረገድ ለሚሰጠው አገልግሎት 0 ነጥብ 75 በመቶ የአገልግሎት ክፍያ የሚከፈልበት እንዲሁም የስድስት ዓመት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በ38 ዓመታት ውስጥ ተከፍሎ የሚጠናቀቅ መሆኑን አስረድተዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ የብድር ስምምነቱን አስመልክቶ ከምክር ቤት አባላት ለቀረቡ ጥያቄዎች በሰጡት ማብራሪያ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከዓለም አቀፍ አበዳሪ ድርጅቶች ያገኘውን ድጋፍና ብድር የያዘ ተጨማሪ በጀት በቅርቡ ለምክር ቤቱ አቅርቦ እንደሚያስጸድቅ ጠቁመዋል።

ተጨማሪ በጀቱ ለዝቅተኛ ተከፋይ የመንግሥት ሠራተኞች ለሚደረግ የደመወዝ ጭማሪ እንዲሁም ለነዳጅ፣ ለዘይት፣ ለማዳበሪያ እና መድኃኒት ድጎማ የሚውል መሆኑን ሚኒስትሩ አስታውቀዋል።

ምክር ቤቱም በብድር ስምምነቱ ላይ ከተወያየ በኋላ የቀረበው አዋጅ 1345/2016 ሆኖ በአንድ ተቃውሞ፣ በአንድ ድምጸ ተአቅቦ በአብላጫ ድምጽ ጸድቋል፡፡

# ሁለቱ ክልሎች ከዓምናው የተሻለ ምርት ለማግኘት በትኩረት እየሠሩ መሆናቸውን ገለጹ

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በ2016/17 የመኸር ምርት ዘመን ከዓምናው የተሻለ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየሠሩ መሆኑን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና የትግራይ የክልሎች ገለጹ፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ባበኸር ኃሊፍ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በክልሉ በ2016/17 ዓ.ም የመኸር ወቅት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሁሉንም የእርሻ መሬት በዘር የመሸፈን ሥራ እየተሠራ ነው፡፡

በ2016/17 የመኸር ምርት ዘመን አንድ ሚሊዮን 308 ሺህ 77 ሄክታር መሬት በዘር በመሸፈን አርባ አምስት ሚሊዮን 184 ሺህ ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በምርት ዘመኑ በሰብል ለመሸፈን ከታቀደው አንድ ሚሊዮን 308 ሺህ 77 ሄክታር ውስጥ 917 ሺህ 294 ሄክታሩ ታርሷል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከዚህ ውስጥ ከ854 ሺህ 418 ሄክታር መሬት በላይ በዘር ተሸፍኗል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም የክልሉን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ሶስት መቶ ሰባ ሺህ 229 ሄክታር መሬት በኩታ ገጠም እርሻ በዘር በመሸፈን አስር ሚሊዮን አርባ ስምንት ሺህ 566 ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ባበኸር፤ ከ370 ሺህ 229 ሄክታር መሬት ውስጥ 53 ሺህ 705 ሄክታር የሚሆነው መሬት በኩታ ገጠም በዘር መሸፈኑን ተናግረዋል፡፡

በትግራይ ክልል በግብርና ቢሮ የሰብል ልማት ቡድን መሪ አቶ ኃይሌ ዓባይ በበኩላቸው፤ በክልሉ አንድ ነጥብ ሶስት ሄክታር መሬት በተለያዩ አዝርት በመሸፈን ሃያ አራት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በክልሉ ለአርሶ አደሮች አስፈላጊውን ግብዓት በማሟላት ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ይህም ምርቱ ተሰብስቦ ጎተራ እስኪገባ ድረስ ድጋፉና ክትትሉ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ አመላክተዋል፡፡

# 222 ወረዳዎች ተለይተው የወባ በሽታ ቅኝትና ክትትል እየተደረገ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ 222 ወረዳዎች ተለይተው የወባ በሽታ ቅኝትና ክትትል እየተደረገ ነው ሲል የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የጤና ሚኒስትር ዶክተር መቅደስ ዳባ ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ የወባ በሽታ ስርጭት ከመስከረም እስከ ታህሳስ እና ከመጋቢት እስከ ግንቦት ባሉት ወራት ጫናው ይጨምራል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በ222 ወረዳዎች ተለይተው የወባ በሽታ ቅኝትና ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

ባለፈው አንድ ወር 700 ሺህ የወባ ህሙማን ህክምና እንደተሰጣቸው ጠቅሰው፣ ከ6 ሚሊዮን በላይ ህሙማንን ማከም የሚችሉ የጸረ ወባ መድኃኒት መሰራጨቱንና ሰባት ሚሊዮን በላይ ፈጣን መመርመሪያ ኪት ወደ ሀገር ውስጥ መግባታቸውን ተናግረዋል፡፡

ወረርሽኙን ለመከላከል 551 ሺህ ተጨማሪ አጎበሮች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው እየተሰራጩ እንደሚገኝ ገልጸው፣ ባለፉት ቀናት አንድ ነጥብ ስምንት ቤቶች ላይ የኬሚካል ርጭት መካሄዱን ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በ 152 ወረዳዎች ላይ በተደረገ የኮሌራ በሽታን የመቆጣጠር ሥራ 109 ወረዳዎች ነጻ ማድረግ መቻሉን ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት 43 ወረዳዎች ላይ ክትትል እየተደረገባቸው እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በ 444 ወረዳዎች ላይ የነበረውን የኩፍኝ ወረርሽኝ በተደረገው ክትትል ከ422 ወረዳዎች ላይ ነጻ ማድረግ ተችሏል ያሉት ዶክተር መቅደስ፣ በቀሪ 22 ወረዳዎች ላይ የመቆጣጠር ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኝ አመላክተዋል።

በተጨማሪም በጥቂት ሳምንታት በተደረገ አሰሳ ምንም አይነት ክትባት አግኝተው የማያውቁ 600 ሺህ ህጻናትን ማግኘት መቻላቸውን ተናግረዋል፡፡

በተያያዘም የጸጥታ ችግር ባለባቸው የተለያዩ አካባቢዎች መንግሥት የህክምና መድኃኒቶች ለዜጎች እያቀረበ እንደሚገኝም ተናግረዋል፡፡

ህብረተሰቡ የሚቀርቡለትን የህክምና መድኃኒቶች ሊጠቀምባቸው እንደሚገባ ጠቅሰው፣ የጸጥታ ችግር ባለባቸው የተለያዩ አካባቢዎች ላይ የህክምና መድኃኒትን ጨምሮ ግብዓቶች እየቀረቡ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አብዱልቃድር ገልገሎ በበኩላቸው፤ የጸጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ከ3 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ መድኃኒቶች ተሠራጭተዋል፡፡

የጸጥታ ችግር ባለባቸው የአማራ፣ በቤኒሻንጉልና ኦሮሚያ ክልሎች ላይ በተለየ ሁኔታ የመድኃኒት ስርጭት እየተካሄደ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ባለፉት ወራት ከ3 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ መድኃኒቶች ተሠራጭተዋል ብለዋል፡፡

በአማራ ክልል በባህርዳር፣ ጎንደርና ደሴ፣ በቤኒሻንጉል አሶሳ ቅርንጫፎች ላይ መሰራጨታቸውን ጠቅሰው፣ የአየር ትራንስፖርትን በመጠቀም ጭምር የክትባት፣ የኤችአይቪ፣ ቲቢ፣ የወባና ሌሎች አስፈላጊ መድኃኒቶች መሰራጨታቸውን ገልጸዋል፡፡



ዶክተር መቅደስ ዳባ

# የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሀገራችን ባንኮች ደግሞ፣ በአገልግሎት ዘመናቸው ውድድር ምን እንደሆነ የሚያውቁ ይመስለኛል ያሉት ክቡር፣ ባንኮቻችን የሚሰጡት አገልግሎት ከእለት ወደ እለት እየተሻሻለ መምጣቱን ይገልጻሉ:: በተለይም በዲጅታል የባንክ አገልግሎት ከፍተኛ ለውጥ እንደመጣ አንስተው፣ ባንኮቹ ከውጭ ሀገር ባንኮች ጋር ተወዳዳሪ ሆነው ለመዝለቅ የሚያቅታቸው አይደሉም የሚል አስተያየት ይሰጣሉ::

የባንክ ከፍተኛ ባለሙያውና በዘምዘም ባንክ የዲጂታል አገልግሎት እና ትራንስፎርሜሽን ዳይሬክተር አቶ ነጂብ አህመድ በበኩላቸው፣ የባንኮች ወደ ሌሎች ሀገራት ወጥተው መሥራታቸው ዓለምን ወደ አንድ የንግድና የኢኮኖሚ ቀጣና ለማምጣት በሀገራት መካከል የተፈረመው የግሎባላይዝሽን ስምምነት አንዱ አካል እንደሆነ ይጠቅሳሉ:: የውጭ ባንኮች ወደ ሀገራችን መጥተው ቢሠሩ በርካታ ጠቀሜታ እንደሚያስገኝም ይናገራሉ:: እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፣ የውጭ ባንኮች ካላቸው የካፒታል አቅም የተነሳ የኢትዮጵያ ባንኮች ማበደር የማይችሉትን ትልልቅ ብድር ሊያበድሩ ይችላሉ:: ይህም ንግድን ያሳልጣል፣ ለዜጎችም አዳዲስ የሥራ እድሎችን ይፈጥራል:: ባንኮቹ ይዘውት የሚመጡት ዘመናዊ እውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማምጣት ጠቀሜታ ይኖረዋል::

የውጭ ባንኮች ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ አቅም ስለሚኖራቸው፣ የውጪ ንግድ ላይ ለሚሠሩና ለመሥራት ፍላጎት ላላቸው ነጋዴዎች የውጭ ምንዛሪን በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ችግር ያላቅቃሉ::

ሌላው የውጭ ባንኮች ወደ ሀገር የመግባታቸው ጠቀሜታ ተወዳዳሪነትን ከፍ በማድረግ የህብረተሰቡ አማራጭ በማስፋትና የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል::

ከፖለቲካ አንጻርም መንግሥት ባንኮቹ ከመጡበት ሀገር ጋር የሚኖረውን የዲፕሎማሲና የልማት ትስስር የማጠናከር እድልን ይፈጥራል:: ከሌሎች ሀገራት ወደ ሀገራችን ገብተው ማልማት የሚፈልጉ ኢንቨስተሮችንም ፍላጎት በመጨመር ረገድ ባንኮቹ ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል ሲሉ ያስረዳሉ::

አቶ ነጂብ ባንኮች ከላይ የተዘረዘሩ ጥቅሞችን የሚያስገኙ ሆነው ሳለ፣ ጉዳትም እንዳላቸው ያነሳሉ:: እርሳቸው እንዳሉት ጉዳቱ እነዚህ ባንኮች ሠርተው የሚያኙት ትርፍ ወደ ራሳቸው ሀገር የሚሄድ መሆኑ ነው:: ይህም በኢትዮጵያውያውያን መያዝ ያለበትን ገበያ እንዲቀራመቱ ያደርጋል:: ይህ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ደግሞ የኢትዮጵያ ባንኮች ተወዳዳሪና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት በመስጠት አብዛኛው ትርፍ ሀገር እንዲቀር ጠክረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል:: ከዚህ አንጻር ከሀገር ውስጥ ባንኮች ዘንድ ካፒታልን ማሳደግና መጠናከር የውዴታ ግዴታ ይሆናል::

ከፍተኛ የባንክ ባለሙያ የሆኑትና በኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ የኮርፖሬት የደንበኞች ትስስር ኃላፊ አቶ ደሳለኝ ሙሉጌታ በበኩላቸው የውጭ ባንኮች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ቢሠሩ አዳዲስ እውቀትና ቴክኖሎጂ አሠራር ይዘው እንደሚመጡ ይገልጻሉ:: ይህን ለባንክ አገልግሎት ሥርዓቱ መልካም መሆኑ አያጠያይቅም ነው ያሉት:: ከዚህ በተጨማሪ በአሁኑ ጊዜ የሀገራችን ባንኮች ማነቆ የሆነውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚቀርፍም ይጠቅሳሉ::

በባንኮች መካከልም ተወዳዳሪነትን በማሳደግ በኩል የባንኮቹ ወደ ሀገር ገብቶ መስራት ሚና እንደሚኖረው የተናገሩት አቶ ደሳለኝ፣ በባንኮች መካከል ወጥ የሆነ የመወዳደሪያ መስፈርት እንዲበጅ በማድረግ በኩልም ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን አንስተዋል::

ባንኮቹ ወደ ሀገር ገብተው መሥራት ሲጀምሩ፣ የሀገር ውስጥ ባንኮች ተወዳዳሪነታቸውን ለመጨመር ጥረታቸውን መጨመራቸውም ሆነ አሠራራቸውን የበለጠ ማዘመናቸው አይቀርም ያሉት አቶ ደሳለኝ፣ ይህም ለሀገራችን የፋይናንስ ሥርዓት መዘመን፣ ለባንኮች የካፒታል እድገትና ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ትልቅ ጠቀሜታ የሚኖረው ይሆናል የሚል ተስፋቸውን ገልጸዋል::

ምሁራኑ በሰጡት አስተያየት የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በባንኩ ዘርፍ መሳተፋቸው ተግዳሮት እንዳለው ሁሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ባንኮችን ከማሳደግ፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ከመፍታትና የሥራ ዕድልን ከመፍጠር አኳያ ዕድሎችን ይዘው የሚመጡ መሆናቸውን ነው ያብራሩት::

# 78 ዓመታትን በስኬት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በቅርቡም የአቪዬሽን ኦስካር ተብሎ በሚጠራው የስካይትራክስ መድረክ ለሰባተኛ ጊዜ የአፍሪካ ምርጡ አየር መንገድ በመባል ክብርን ተቀዳጅቷል:: የአፍሪካ ምርጥ የቢዝነስ ክፍል የኢኮኖሚ ክፍል አየር መንገድ ለስድስተኛ ጊዜ እንዲሁም በአፍሪካ የኢኮኖሚ ክፍል ምርጥ ምግብ አገልግሎት ሰጪ አየር መንገድ በመባል ተደራራቢ ዕውቅና ተቀናጅቷል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ በ2016 በጀት ዓመት ሰባት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቱ፣ 17 ነጥብ አንድ ሚሊዮን መንገደኞችን ማጓጓዙ፣ 754 ሺህ 681 ቶን ካርጎ ማጓጓዙ፣ አምስት ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያዎችን ወደ ሥራ ማስገባቱ እና ሌሎች በርካታ ስኬቶችን ማስመዝገቡ የሚታወስ ነው:: የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ስኬታማ ሆኖ የዘለቀበትን ምክንያት ዙሪያ ምሁራን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

የአፍሪካ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ተንተኙ ላውረንስ ፍሪማን በበኩላቸው እንደሚሉት፤ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ብዙ ጊዜ ተጉዣለሁ። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያውያን በርካታ ጥቅሞች አለው:: አየር መንገዱ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ ባለፈም ለመላ አፍሪካውያን ኢኮኖሚያዊ እድገት አዎንታዊ ሚና ይጫወታል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለሰባት ተከታታይ ዓመታት በአፍሪካ አንደኛ አየር መንገድ ሆኖ እውቅና አግኝቷል። ይህም በአፍሪካ ውስጥ ሊተገበር የሚችል ብዙ ተጨማሪ አቅም እንዳለ ማሳያ ነው:: የኢትዮጵያ አየር መንገድ 139 ዓለም አቀፍ የመንገደኞች መዳረሻዎች አሉት:: ከእነዚህ ውስጥ 63ቱ በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ናቸው:: ይህ የሚያሳየው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ነው ይላሉ::

ተንታኙ እንደሚሉት፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለኢትዮጵያ እና ለአካባቢው የኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ሆኖ ሳለ በኤርትራ ሲቪል አቬሽን ባለሥልጣን የሚደረገው ስም ማጥፋት አየር መንገዱን ለማዳከም፣ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻከር ያለመ ስለመሆኑ ያስረዳሉ::

በኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ላይ የሚካሄደው የስም ማጥፋት ዘመቻም ማንንም የሚጠቅም ባለመሆኑ መስተካከል እንዳለበት ይገልጻሉ::

ባለፉት ዓመታት እንኳን የነበረው ከስድስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ዓመታዊ ገቢ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል:: አየር መንገዱ ከኢትዮጵያ አልፎ ለአህጉሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት ጉልህ ሚና አለው ይላሉ::

ሌላኛው የኢኮኖሚ ባለሙያ እና የፖሊሲ አማካሪው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገራት ጋር በቱሪዝም፣ በንግድ፣ በኢንቨስትመንት እና በሌሎች ዘርፎች ያላት ግንኙነትን ለማጠናከር ጉልህ ሚና አለው ይላሉ::

እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ገለጻ፣ አየር መንገዱ ዓለም አቀፍ እና የሀገር ውስጥ መዳረሻዎችን እያስፋፋ ነው:: ይህ ደግሞ ተጨማሪ ቱሪስቶችን ወደ ሀገሪቱ ለመሳብና የንግድ ሥርዓቱን ለማስፋፋት እንደሚያግዝ ይናገራሉ::

ለአብነት በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና የንግድ እቃዎች በአብዛኛው በባቡር እና በአውሮፕላን ነው የሚጓጓዙት:: ለዚህ ደግሞ በአፍሪካ ውስጥ እንደ ኢትዮጵያ የተደራጀ የአየር መንገድ መሠረተ ልማት ያለው ሀገር ስለሌለ ትልቁን ድርሻ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ይወስዳል ሲሉ ያስረዳሉ::

በኮቪድ ጊዜም የህክምና ግብዓቶችን ጨምሮ ሌሎች የካርጎ ጭነቶችን ሲያጓጉዝ የነበረው የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንደነበር ያስታውሳሉ::

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአቬሽን ዩኒቨርሲቲ መክፈቱ፣ የጥገና ቦታቸውን በማስፋፋት የሌሎች ሀገራትን አውሮፕላን ጭምር መጠገን መጀመራቸው እና ሌሎች በርካታ ሥራዎችን መሥራታቸው የሚበረታታ ነው ይላሉ::

አየር መንገዱ በቀጣይ የአውሮፕላኖቹን ቁጥር በመጨመር፣ የተቋሙን ሠራተኞች የቴክኖሎጂ አጠቃቀም በማሳደግ፣ መዳረሻ ሀገራትን በማስፋፋት እና ሌሎች ሥራዎችን በትኩረት በመሥራት ስኬታማነቱን አጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ያስረዳሉ::

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን ጣሰው ፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ለ78 ዓመታት በስኬት ተጉዟል:: በቀጣይም እድገቱን ለማፋጠን የሚረዱትን በርካታ ሥራዎች እያከናወነ ነው ይላሉ::

አየር መንግዱ እያደገ የመጣውን የአየር ትራንስፖርት ፍላጎት ለማሟላት 125 አውሮፕላኖችን አዟል:: ካዘዛቸው 125 የአውሮፕላኖች መካከል 105ቱ የታዘዙት በታህሳስና የካቲት 2016 ዓ.ም ሲሆን፤ 20ዎቹ ቀደም ብለው የታዘዙ መሆናቸውን ይናገራሉ::

የ105ቱ አውሮፕላኖች የመረከቢያ ጊዜ እ.ኤ.አ ከ2027 እስከ 2030 ባሉት ጊዜ ውስጥ መሆኑን በመግለጽ፤ በ2017 በጀት ዓመት ደግሞ ቀደም ብለው ከታዘዙት 20 አውሮፕላኖች መካከል 16ቱን ወደ ሥራ ለማስገባት እና 20 ሚሊዮን መንገደኞችን ለመጓጓዝ አቅዶ እየሠራ መሆኑን ያስረዳሉ::

ከዚያ ወደህ ከፍተኛ የሆነ የአውሮፕላን ፍላጎት ቢኖርም አውሮፕላን በፍጥነት ማግኘት ፈተና ስለመሆኑ ያመላክታሉ::

በሌላ በኩል በግንባታ ላይ ያሉ አምስት የአውሮፕላን ማረፊያዎችን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ እየሠራ ሲሆን፤ አውሮፕላን ማረፊያዎቹ ያቤሎ፣ ሚዛን አማን፣ ደብረ ማርቆስ፣ ጎሬ መቱ እና የነገሌ ቦረና መሆናቸውን ያስረዳሉ::

ሥራ አስፈጻሚው እንደሚሉት፣ የያቤሎ አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ 54 በመቶ፣ የሚዛን አማን አውሮፕላን ግንባታ ደግሞ 64 በመቶ ደርሷል:: ግንባታቸውንም ታህሳስ 2017 ዓ.ም ላይ ለማጠናቀቅ እየተሠራ ነው ይላሉ::

የደብረ ማርቆስ አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ሥራ ተጀምሮ በጸጥታ ምክንያት ተቋርጦ የነበረ ቢሆንም አሁን ላይ ግንባታው ተጀምሮ መጋቢት 2017 ዓ.ም ለማጠናቀቅ እየተሠራ ስለመሆኑ ይናገራሉ::

የነገሌ ቦረና አውሮፕላን ማረፊያም መጋቢት ላይ የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ ጎሬ መቱ የአውሮፕላን ማረፊያም ደግሞ አንድ ዓመት ጊዜ ሊወስድ ይችላል ይላሉ::

የመንገደኛ መስተናገጃ ተርሚናል እና የአውሮፕላን መንደርደሪያ ግንባታን በሚመለከት በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው የሚሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ቀደም ሲል ከተጀመሩት አምስት የሀገር ውስጥ መንገደኞች መስተናገጃ ተርሚናሎች መካከል ጎዴና ጂንካ ተጠናቀው ተመርቀዋል:: ሮቤ ግንባታው ተጠናቆ ምረቃ እየጠበቀ ነው::

የደምቢዶሎ፣ የነቀምት፣ የአክሱም፣ እና የሰመራ አውሮፕላን ማረፊያ የአውሮፕላን መንደርደሪያዎች ማስፋፊያ ግንባታ ተጠናቀው ሥራ ላይ ስለመዋላቸውም አንስተዋል::

በተያዘው የ2017 በጀት ዓመት የሀገር ውስጥ አውሮፕላን ማረፊያዎችን ደረጃ ለማሻሻልና የሚጎሏቸውን መሠረተ ልማት ለማሟላት እንዲሁም የቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የሀገር ውስጥ ተርሚናሉ ላይ ተጨማሪ የማስፋፊያ ሥራ ለመሥራት በጀት ስለመመደቡ ይገልጻሉ::

አዳዲስ የመንገደኛ ተርሚናል ለመገንባት የታሰበባቸው ቦታዎች ሽሬ፣ ነቀምትና ደምቢዶሎ ሲሆኑ፤ በወላይታ ሶዶ ደግሞ አዲስ አውሮፕላን ማረፊያ ለመገንባት እንቅስቃሴ ጀምረናል ይላሉ::

በተያዘው በጀት ዓመት አምስት ዓለም አቀፍ የአውሮፕላን መዳረሻዎችን ለመጨመር ታቅዶ አንዱ ወደ ሥራ የገባ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ በቀጣይ ጊዜያት ይገባሉ:: ከዚህ በተጨማሪም ጥናት ላይ የተመሠረተ አዳዲስ ጣቢያዎች እንከፍታለን ሲሉ ይናገራሉ::

የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ለማሳደግ፣ ለማዘመን እና እያደገ የመጣውን የአየር ትራንስፖርት ፍላጎት ለማሳካት በትኩረት እንደሚሠሩ ጠቁመዋል::

ምሁራኑ በሰጡት አስተያየትም የኢትዮጵያ አየር መንገድ በመጪዎቹ ዓመታት በአፍሪካም ሆነ በዓለም ግንባር ቀደም ተጠቃሽና ስኬታማ ሆኖ የሚቀጥል መሆኑን ይገልጻሉ::

# አደጋን የመከላከል አቅም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሊዘንብ እንደሚችል ትንበያ እንደነበር የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን መረጃ ያሳያል::

የዘርፉ ባለሙያዎች ችግር ያለባቸውን አካባቢዎች በጥናት መለየትና ዘላቂ መፍትሄ ማስቀመጥ ያስፈልጋል ይላሉ:: ለረጅም ዓመታት እንዲህ አይነት አደጋ ተሰምቶ ባይታወቅም የሁኔታዎች መለዋወጥ ክስተቱን ተደጋጋሚ እንዳያደርገው ቅድመ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባም ያሳስባሉ::

የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ በየአካባቢው ከፍተኛ ዝናብ መዝነቡን ተከትሎ የወንዝ ሙላትና አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል የተተነበየው ነገር እየተከሰተ ነው::

በተዳፋት አካባቢዎችና በወንዞች ዳርቻ የሚገኝ ማህበረሰብ ትልቅ ጥንቃቄ እንዲያደርግ፤ በየደረጃው የሚገኙ በአስተባባሪ ኮሚቴዎች ተጋላጭ አካባቢዎችን ለይተው እንዲሠሩ አቅጣጫ ተቀምጦ እየተከናወነ እንደሚገኝም ይጠቁማሉ::

ከሠብዓዊ ድጋፍ ጎን ለጎን በዘላቂነት የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች በተደራጀና በባለሙያ ጥናት በሚለይ ቦታ ለማከናወን ጥናቶች እየተሠሩ ናቸው፣ እንዲህ አይነት ክስተት ሲያጋጥሙ ለነፍስ አድን የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሌላ የከፋ ጉዳት የማያስከትሉ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ ጎፋ ላይ የተመለከትነው ይህንን ነው ይላሉ::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህርና ተመራማሪ ጌትነት መዋ (ዶ/ር)፤ ሰሞኑን አደጋ ያስተናገደው አካባቢ ለም፣ ከዓመት ዓመት ዝናብ የማያጣው መሆኑን ይገልጻሉ::

49 በመቶ የኢትዮጵያ መሬት ለዚህ አይነት ችግር ተጋላጭ በመሆኑ ሰፊ ሥራ እንደሚጠይቅ ጠቁመው፣ ለውሳኔ ሰጪ አካላት በሚጠቅም መልኩ አካባቢዎችን በደንብ ማወቅ፣ መለየትና ለችግሮቹ መፍትሄ ለማምጣት የሚያስችሉ ዝርዝር ጥናቶች ሊደረጉ እንደሚገባም ያሳስባሉ::

ህብረተሰቡ ለመደጋገፍና ለመተጋገዝ የሚያደርገውን ጥረት የሚያሳይና የሚደገፍ ቢሆንም ትብብር ሲደረግ ተጨማሪ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ይላሉ::

እንዲህ አይነት ችግር ባለባቸውና ለአደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ ተዳፋት በሆኑ፣ በወንዝ ዳርቻዎች ጉድጓዶች፣ ወንዞች፣ ረግረጎች አካባቢ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል:: የነፍስ ማዳን ተግባሩም ቢሆን ከየአካባቢው የጸጥታ መዋቅር ጋር በመመካከር የሚሠራ መሆን እንዳለበትም ነው አምባሳደር ሽፈራው (ዶ/ር) የሚያሳስቡት::

ጌትነት (ዶ/ር) የመሬት መንሸራተት ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም በኢትዮጵያ ሁኔታ ለመሸርሸር አመቺ የሆነ አፈር ወይም የበሰበሰ ድንጋይ ከጠንካራው አለት በላይ በዛ ብሎ መቀመጥ አንዱ ምክንያት መሆኑንም ይጠቁማሉ::

የመሬት ተዳፋት መሆን ከፍተኛ የዝናብ መጠን መዝነብን ተከትሎ ለመሬት መሸርሸር ዝግጁ የሆነ አፈር ውሃውን ይጠጣውና በግፊት ቁልቁል የመንሸራተት ክስተት እንደሚፈጥርም ያመለክታሉ::

የሰዎች ተጽእኖም ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚሉት ተመራማሪው፤ ለመኖሪያና ለእርሻ ሥራ እጽዋትን መመንጠር መሬቱን በቀላሉ ለመሸርሸር ዝግጁ ያደርገዋል ነው የሚሉት:: ላለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር መጨመሩን ተከትሎ ሀብትን ለማግኘት ሁሉም በየአካባቢው ሽሚያ ስለሚያደርግ መሬት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ማሳደሩንም ይጠቁማሉ::

በሙስና፣ በግዴለሽነት፣ በእውቀት ማነስም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች በመሬት አጠቃቀም ላይ የወጡ ሕጎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች አለመፈጸማቸው መሬቱ ባለቤት አልባና ለዚህ አይነት ችግር ተጋላጭ እንዲሆን እንዳደረገው ተመራማሪው ይጠቁማሉ::

በሀገር ደረጃ በመሰል የተፈጥሮ አደጋ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ሰው በተከለለው ደግሞ እስከ 800 ሺህ ማህበረሰብ ሊያፈናቅል እንደሚችል መተንበዩን የሚያመለክቱት ሽፈራው (ዶ/ር) ፤ በየክልሉ ግምት የተወሰደባቸው አካባቢዎች ላይ ኮሚቴ ተቋቁሟል ታክስ ፎርሶችም እየሠሩ ይገኛሉ ይላሉ::

አምባሳደር ሽፈራው (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ ገዛ ጎፋ ላይ ካሉት 29 ቀበሌዎች 15 ቀበሌዎች የተጋላጭነት ደረጃቸው በድሮን፣ በሜትሮሎጂ ባለሙያዎችና በጂዮሎጂስቶችና በጂዮስፓሻል ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት ዳሰሳ እየተሠራ ነው:: በዳሰሳው የሚገኙ መረጃዎች ላይ በመመሥረት በተጨማሪነት የመልሶ ማስፈርና ሌሎች ሥራዎች ይሠራሉ::

ጌትነት (ዶ/ር) የአደጋ አካባቢውን በትክክል ለይቶ ህብረተሰቡ የት ቦታ መስፈር እንዳለበት መወሰን፤ አካባቢውን ከእዚህ ችግር መቅረፍ የሚቻለው ምን አይነት ተግባር በማከናወን እንደሆነ ማሰብ እና በሳይንሳዊ መንገድ ብዙ ውሃ ሊመጡ የሚችሉ የዛፍ አይነቶችን ለይቶ በአካባቢው መትከል ይገባል ነው የሚሉት::

የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ በአግባቡ በመሥራት የችግሩን ተጋላጭነትን መቀነስ ይገባል የሚሉት ጌትነት ዶ/ር፤ በገጠር የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን አማራጭ ገቢ የሚያገኙበትን ሁኔታ በመፍጠር በመሬት ላይ ጥገኛ የሚሆኑበትንና መሬት የሚጎዳበትን ሁኔታ መቀነስ ያስፈልጋል ሲሉ ይመክራሉ::

አምባሳደር ሽፈራው (ዶ/ር) የፌዴራል መንግሥት ሁሉም ዘርፎች ከክልሎች ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ ጊዜ ስጋት ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል ተቋቁሟል:: ከተጋላጭ አካባቢዎች ማህበረሰቦችን ለማውጣት እየተሠራ ነው፤ እስካሁን ስድስት ሺህ 600 ሰዎች ተለይተዋል:: የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ የጋራ ትብብር እንዲኖር የዝግጅት ሥራዎች ሲከናወኑ መቆየታቸውን ይጠቁማሉ::

አያይዘውም፤ ተፈጥሯዊም ሰው ሠራሽም አደጋዎች የመከሰታቸው ሁኔታ ዓለም አቀፍ ባህሪ ነው:: አቅም ባላቸው ሀገሮች ጭምር ይህ ሁኔታ ፈተና ነው:: የመሬት መንሸራተት፣ የጎርፍ አደጋ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም የእሳት አደጋ ባልታሰበ ሰዓት ሊከሰት ይችላል:: እነዚህን አደጋዎች ቀድሞ ለይቶ መዘጋጀትን የሚጠይቅ አቅም እየገነቡ መሄድ ይገባል ሲሉ ሃሳባቸውን ይጠቀልላሉ::

# ርዕሰ አንቀፅ

## የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የተጀመረውን ልማት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ያስችላል!

በኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥ ከመጣበት ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከ7 በመቶ በላይ እያደገ መሄዱን መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በተለይም ሀገሪቱ በበርካታ ውስብስብ ችግሮች ውስጥ ባለችበት በዚህ ወቅት ይህን መሰል ዕድገት ማስመዝገብ መቻሏ እንደ ሀገር ጠንካራ ሥራ መሠራቱን የሚያመላክት ነው::

ቀላል የማይባለው የሀገሪቱ ክፍል በጦርነትና በጸጥታ ችግር ውስጥ ሆኖ በቆየበት ወቅት ሁሉ ከስድስት በመቶ በላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ መቻሉ ከለውጡ ወዲህ የተቀየሱ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ውጤታማ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው::

ከለውጡ ወዲህ ኢትዮጵያ በታሪኳ አይታ የማታውቀውን በተከታታይ ከወጭ ንግድ ከ4 ቢሊዮን ዶላር በላይ አግኝታለች:: ሀገሪቱ ፍጹም ሰላም በነበረችባቸው ዓመታት እንኳን ከወጭ ንግድ ሲገኝ የነበረው ዓመታዊ ገቢ ቢበዛ ከ 3 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር ዘልሎ አያውቅም::

ከ2010 ዓ.ም በኋላ ተግባራዊ መደረግ የጀመረው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ኢትዮጵያ ያሏትን ሀብቶች እንድታጤንና ለውጭ ገበያም በስፋት እንድታቀርብ ዕድል ከመክፈቱም ውጪ በከፍተኛ ወለድ ስትበደር የነበረበትን አካሄድ በማቆም በአንፃሩ የልማት አጋሮቹ ከሆኑት ዓለም አቀፍ ተቋማትና ከመንግሥታት ትብብር በአነስተኛ ወለድ ለረጅም ጊዜ በሚሰጡት ብድሮች ላይ ትኩረት አድርጎ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል::

ሆኖም አሁን ያለው የልማት ፍላጎት በዚህ ብቻ የሚሳካ አይደለም:: ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን እና የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰትን የሚጠይቅ ነው:: ከዚህም በላይ በሀገር ውስጥ የገንዘብ ፍሰትን ማሳለጥና የውጭ ምንዛሬን በገበያው እንዲመራ ማድረግም አስፈላጊ የሆነበት ወቅት ላይ ደርሰናል::

ስለዚህም ወቅቱን በሚዋጅ መልኩ ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥርዓት ውስጥ መግባት የግድ ሆኗል:: ይህን መሠረት በማድረግም ከሀምሌ 22 ጀምሮ ኢትዮጵያ ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ የገባች ሲሆን ይህም ሀገሪቱ ለጀመረችው የኢኮኖሚ ብልጽግና ትልቅ አቅም ይሆናል የሚል እምነት ተጥሎበታል::

የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ ገቢ በሚያስገኙ ዘርፎች የተሠማሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ይጠቅማል:: ወደ ውጭ የሚላኩ እንደ ቡና፣ ሰሊጥ፣ የቅባት እህሎች፣ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ጫት የመሳሰሉ ሸቀጦችን የሚያመርቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ገበሬዎች፣ የቁም እንስሳትና ሥጋ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ አርብቶ አደሮችና ነጋዴዎች፣ በወጪ ንግድ ዘርፍ የተሠማሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የፋብሪካ ሠራተኞች፣ በማዕድን ፍለጋ ላይ የተሰማሩ በርካታ ዜጎችና አምራቾች፣ በሆቴልና በቱሪዝም ዘርፎች የተሠማሩ በሺህ የሚቆጠሩ ነጋዴዎች፣ በውጭ ሀገር ከሚኖሩ ዘመዶቻቸው/ ጓደኞቻቸው የውጭ ምንዛሪ የሚላክላቸው በሚሊዮን የሚገመቱ የሐዋላ ተጠቃሚዎች እንዲሁም ከውጭ ገንዘብ ፈስስ የሚደረግላቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ተቋማት፣ ከእነዚህም ጋር በሽርክና የሚሠሩና ምርት የሚያቀርቡ ሌሎች አካላት የዚህ የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ በማድረግ ጤናማ የገንዘብ ፍሰት እንዲኖር ያስችላል:: ይህ መሆኑ ደግሞ ሀገሪቱ ጠቀም ያለ የውጭ ምንዛሬ እንድታገኝ በማድረግ ተስተጓጉለው የነበሩ ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችና የልማት ጥያቄዎች እንዲፈቱ ያስችላል::

ከዚሁ ጎን ለጎንም የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን ያበረታታል፤ የማምረት ሥራቸውን እንዲያስፋፉና የገበያ ድርሻቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል::

መመዘኛውን የሚያሟሉ የውጭ ኢንቨስተሮችም በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ (Ethiopian Securities Exchange) እንዲሳተፉ በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ፍሰትን እንዲጨምር ያደርጋል:: በልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ የሚሠሩ ኩባንያዎች የውጭ ምንዛሪ ገቢያቸውን ሙሉ በሙሉ ለራሳቸው መያዝን ጨምሮ ልዩ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም መብት የሚያናጽፋቸውም በመሆኑ ገንዘባቸውን በሀገር ውስጥ እንዲያፈሱ ያነሳሳቸዋል:: በምትኩም በሀገር ውስጥ የውጭ ምንዛሬ ፍሰት እንዲጨምር ያደርጋል::

ከሁሉም በለላይ ደግሞ የዓለም አቀፍ አበዳሪ ተቋማትና ሀገራት አቋርጠውት የነበረውን ርዳታ እና ብድር እንዲለቁና ኢትዮጵያም ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የምታገኘውን ብድርና ርዳታም ቀጣይነት እንዲኖረው ያስችላል:: ይህ ማለት ደግሞ በፋይናንስ እጥረት የቆሙ የልማት ውጥኖች እንዲተገበሩና ኢትዮጵያ የጀመረችው ዕድገት ወደ ላቀ ደረጃ እንዲደርስ ያስችላል::

በአጠቃለይ የሀገር በቀል ማሻሻያ ሥርዓቱ ቀጣዩን የኢትዮጵያን የዕድገት ደረጃ ከፍ እንዲል ከማድረጉም ባሻገር ከቀረው የዓለም ሀገራት ጋር ያላትን እና እያደገ የመጣውን ትስስር ለማጠናከር የሚረዳ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ ሁሉም ዜጋ የድርሻውን ሊወጣ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።።

## ሥልጣኔን ከግል፣ መዘመንን ከራስ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ሥልጣኔ ከራስ ሲጀምር ፣ ቤተሰብ አካባቢና ሀገር ይዘምናል:: መሠልጠንን ባህል ያደረገ ትውልድ ሲበዛ ደግሞ መልካም እሴቶች ይበረክታሉ፣ የማህበረሰቡ አመለካከትም በአንድ ይቃኛል:: ዛሬ ዓለማችን ለደረሰችበት የዘመን ቴክኖሎጂ አንዱ ለእያንዳንዱ፣ ሌላውም ለብዙሃኑ ያደረገው አስተዋጽኦ ውጤቱን አልቆታል :: ሥልጣኔን አምኖ ለውጥን ከራስ የጀመረ ትውልድ የሚያደርገውን ሁሉ ጠንቅቆ ያውቃልና::

ብዙዎች እንደሚስማሙበት ሥልጣኔ ማለት የሠለጠነ ባህል ወይም ህብረተሰብ ማለት ነው:: እኛ አልፈን በተጓዝናቸው ዘመናት ሁሉ የሥልጣኔ ዐሻራዎቻችን አብረውን ነበሩ:: ጊዜው በሚዋጀውና ትውልዱ በሚሸከመው አቅም ልክም የራሳችን ቀለም ሲንጸባረቅ፣ ሲደምቅ ቆይቷል::

ይህ እውነት ከማንነታችን ተሻግሮ አፍሪካዊ፣ ብሎም ዓለምአቀፋዊ ምልክታችን እንደሆነ ዘልቋል:: እንዲህ መሆኑ ከሌሎች ሲለየንና ሲያኮራን የቆየ ቢሆንም ‹‹ስም ብቻውን›› ህውልት እንደማይሆን ግን ቆይተንም ቢሆን ተረድተናል::

ዛሬ በቆምንበት ዘመን ደግሞ ለሥልጣኔው ግንባር ቀደም ከምንባለው ኢትዮጵያውያን ዓለም ብዙ ቢጠብቅ አያስገርምም:: እንዴትና ለምን የሚል ጠያቂ ቢኖር ደግሞ ምላሹ በብዙ ሊመነዘር ይችላል:: ኢትዮጵያ የሥልጣኔዎች ሁሉ መነሻ፣ የዘመናዊነት ጥንስስ ስለመሆኗ አፍን ሞልቶ መናገር አያሳፍርምና::

በተለያዩ ጊዜያት ስለ ኢትዮጵያ ቀደምትነት የጻፉ የውጭ ሀገራት ዜጎች ይህች ሀገር አሁን ለምንገኝበት ሥልጣኔ በር ከፋች ስለመሆኗ በእማኝነት አረጋግጠዋል:: መላው ዓለም ሥልጣኔ ይሉትን ቃል በወጉ በማያውቀው ቀዳማዊ ዘመን አክሱም ላሊበላን ያቆመ፣ የራሱን ፊደል የቀረጸ፣ በብቸኛ የዘመን ቀመር የቆጠረ፣ ፋሲል ግንብን የመሰሉ ኪነህንጻዎችን ያነጸ፣ ትውልድ ታላቋን ኢትዮጵያ አድምቋት አልፏል::

ዛሬ ከዘመናት በኋላ ይህች ሀገር ልትደርስበት የሚቻላትን ዘመናዊነት ሌሎች ሀገራት ቀድመው ተቆናጠውታል:: በአባቶቹ ታሪክ ‹‹ነበር››ን የሙጥኝ ብሎ የቀጠለው ትውልድ ዳናውን ይዞ አለመከተሉ ዛሬ ኢትዮጵያ ለምትጠራበት የኋላቀርነት ስያሜ አይነተኛ ምክንያት ሆኗል::

ሥልጣኔ በድርጊት ብቻ አይገለጽም:: ዘመናዊነት የሚለካው ከራስ በሚነሳ አመለካካት ጭምር እንጂ:: ውጫዊ ዕድገት በሚታይበት አቋም ውስጣዊ ማንነት አብሮ ካልበለጸገ ደግሞ ዕድገት በእኩል ሊፈጥንና ሊሮጥ አይችልም::

ሥልጣኔን ባህሉ ያደረገ ትውልድ ሁሌም ከስህተቱ ይማራል:: መቼም ቢሆን በራሱ የአዕምሮ ትዕዛዝ ይገዛልና የሌሎችን አስታዋሽነት አይሻም:: ሥልጣኔን ከራሱ ያራቀ ፣ ዘመናዊነትን ሊቀበል የሸሸ ቢኖር ደግሞ መቼም ከስህተት አያልፍምና ከቅጣትና ጸጸት ጋር ሊኖር ግድ ይለዋል::

አብዛኞቻችን ከዕድገታችን ማነስና ከሌሎች ምክንያቶች ጋር ተያይዞ ተለምዷዊ አኗኗርን ፈጥነን ለመተው ስንቸገር ይስተዋላል:: የዘመናዊነት ኑሮ አጠገባችን እያለ እንኳን የኖርንበትን ልማድ ለመተው አቅም አናጣለን:: ይህ እውነት ከፍ ሲል ደግሞ ከራስ አልፎ ለአካባቢ ብሎም ለሀገር ጠንቅ ሲሆን ይታያል::

ተደጋግሞ እንደሚባለው ሥልጣኔ ከአእምሮ ካልመነጨ ዕድገቱ ሙሉ ሆኖ አይቆምም :: አስቀድሞ አስተሳሰብ ላይ ያልተሠራ ዘመናዊነትም በተግባር የሚተረጎም አይሆንም:: በትንሹ አንድ ምሳሌ ላንሳ፤ ስለቆሻሻ አወጋገዳችን:: ተገቢው ገንዳ በወጉ ተቀምጦ ለዓይን የሚከብድ ቆሻሻን በገንዳው ዙሪያ ጥሎ መሄድ ከኋላቀርነትም በላይ ሕገወጥነት ነው:: እንዲህ መሆኑ ግን ከሕግ ተጠያቂነት አያስጥልም:: ዘመናዊነት የገባው ትውልድ ለሕገወጥነት አይዳረግም:: የሚሠራውን ያውቃልና ሁሌም ለሕግና መመሪያ ተገዢ ነው::

አጥፊና ሕግን ተጻራሪ በሌለበት ማስጠንቃቂያ፤ ቅጣትና እስር ይሏቸው አጋጣሚዎች አይኖሩም:: በሥልጣኔ አምኖ ለዘመናዊነት የሚገዛ ትውልድ ደግሞ በትናንሽ ተራ ጉዳይ ተጠያቂ የመሆን አጋጣሚው የጠበበ ነው:: ሕግን የሚያከብር ትውልድ በበዛ ቁጥር ሀገር ትለማለች:: ሕዝብም በዘመናዊነት ጎዳና ተራምዶ በሥልጣኔ መስመር ያብባል::

ከጥቂት ጊዜ ወዲህ በመዲናችን አዲስ አበባ እየታየ ያለው ለውጥ የዘመናዊነት አንዱ መገለጫ ነው:: አሮጌው በአዲስ መተካቱ፣ ለዓይኖች መልካም እይታ መፈጠሩና ፈጣን የሥራ ባህል መዳበሩም በመልካም ጎን የሚታይ እውነታ ነው::

ከዚሁ ለውጥ ጋር ተያይዞ በርካቶች የሥራ ዕድል አግኝተዋል:: አዳዲስ ተግባራዊ ለውጦችም ተስተውለዋል::

ይህ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የፈሰሰበት የሀገር ሀብት በአግባቡ ተጠብቆ ለትውልድ ያልፍ ዘንድ የእያንዳንዱ ነዋሪ ሃላፊነትና ግዴታ መሆኑ አያጠያይቅም:: እነዚህ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ሥራ ሲጀምሩ ሊያጋጥም የሚችል የጥንቃቄ ጉድለት ታዲያ ‹‹ግዴለሽነት›› ተብሎ ብቻ የሚታለፍ አይሆንም::

ዘመናዊነትን ተከትሎ ሥልጣኔን የሚተገብር እንዳለ ሁሉ ለዚህ ደንብ ተገዢ የማይሆን ማንነት ሊኖር እንደሚችልም ይገመታል:: ጥፋት ከመፈጸሙ አስቀድሞ ማስተማርና ማስጠንቀቅ ያለ ቢሆንም ደንቡን ተላልፎ ድርጊቱን የሚፈጽም አካል ሲገኝ ደግሞ ተገቢው ቅጣት ሊተገበር የግድ ይላል::

ሰሞኑን ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያይዞ የሚኖር የሀብት አጠቃቀምና ሕግን በሚጥሱት ላይ የሚከተለው የቅጣት አወሳሰን ደንብ ይፋ ሆኗል:: የከተማዋ የደንብ ማስከበር ባለሥልጣንን ጨምሮ የከተማዋ ትራፊክ ማኔጅመንት በየግላቸው ያወጡት ጠንከር ያለ ሕግ በቅርቡ ተግባራዊ እንደሚሆንም ተጠቅሷል::

በከተማዋ የኮሪደር ልማትና በተሠሩ መንገዶች ላይ ሕግ ተጥሶ ሲገኝ ዕውን የሚሆነው ሕግ ታዲያ አሽከርካሪዎችና እግረኞች ላይ ጭምር የሚተገበር ነው:: እግረኞች፣ አሽከርካሪዎችና ብስክሌተኞች በጋራ ለሚጠቀሙበት መንገድ በእኩል ተናበው በአግባቡ ሊጠቀሙ እንደሚገባ በደንቡ ላይ ተጠቅሷል::

ከዚሁ የመንገድ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚኖር የሕግ ጥሰት በአግባቡ የሚዳኝ ሲሆን ቆሻሻን ባልተገባ ቦታ ጥሎ የሚገኝ ማንኛውም ሰው በተቀመጠው ደንብና መመሪያ መሠረት የገንዘብ ቅጣት እንደሚጣልበት ተገልጧል::

ወደቀደመው መነሻችን እንመለስ ፣ ሥልጣኔን ወዳነሳንበት ርዕሰ ጉዳይ:: ዘመናዊነትን ተግባራዊ ባደረግንበት በአሁኑ ዘመን እንደቀድሞው ማንነታችን በወጉ ያልተከተለን ሥልጣኔ ዛሬ ለዕድገታችን ሳንካ ሆኖ እየፈተነን ይገኛል:: በአንዱ እጃችን ሠርተን በሌላው የምናጠፋበት አጉል ልማድም እየተዋረሰን መሆኑን መደበቅ አይቻልም::

ይህ በአስተሳሰብ የመዘመን እውነት አስቀደሞ ገብቶን ቢሆን ዛሬ ደንብና መመሪያ ወጥቶልን ‹‹በአድርግ፣ አታድርግ›› ሕግ ባልተያዝን ነበር:: ከድርጊቶቻችን ጋር ዘመናዊነትን አውቀን ተግብረነው ቢሆን ለቅጣትና እሱን ይዞ ለሚከተለው ችግርም ባልተጋለጥን ነበር::

የቀደመው ሥልጣኔያችንን ማውራት ፣ መተረኩ ብቻ ለእንደኛ አይነቱ ማንነት ጥቅሙ የሳሳ ነው:: ይልቁንስ የፊቱን ታሪካችንን ይዘን፣ የራሳችንን ዐሻራ አኑረን ለመጪው ትውልድ የሚተርፍ እሴት ብናተርፍ ለሁላችንም የሚበጅ ይሆናል::

እኛ በትናንቱ ደማቅ ታሪካችን ስንኩፈስ የዛኔ ጭራ የተባሉ ሀገራት ዛሬ ቀድመውን ሄደዋል:: ‹‹ሙያ በልብ›› እንዲሉ እነሱ የእኛን ታሪክ መነሻ አድርገው የጀመሩት የሥልጣኔ ጉዞ ፍሬው አብቦ ማንነታቸው ተለውጧል::

አሁንም ቢሆን ካለፈው ልምዳችን ተምረን ውስጣችንን ካዘመንን ማንነታችን የማይለወጥበት፣ ታሪካችን የማይቀየርበት ምክንያት የለም:: በየአጋጣሚው ራሳችንን ለስህተት ዳርገን ፣ በሚወጣብን ደንብና መመሪያ ከመታሰር ይልቅ ሥልጣኔን ወደራሳችን አምጥተን ዘመናዊነትን መተግበር ይቻለናል::

ዛሬም ትናንትናን የነበርን ሕዝቦች ማንነታችን ቀጥሏል:: አብሮን የኖረው የጥንካሬ ዐሻራ ቀለሙ ሳይፈዝ እንዲቀጥል ታሪካችንን ሳንረሳ ሥልጣኔያችንን ልናነሳው፣ መዘመናችንን ልናድሰው ይገባል::

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሺ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ነገረ “የገንዘብ ልውውጥ”

**(Currency Swap)፤**

ዲዶላራይዜሽን ወይም “De-dollarization” የአሜሪካን ዶላር በዓለም አቀፍ ንግድ፣ ፋይናንስ እና ክምችት ላይ ያለውን የበላይነት የመቀነስ ሂደት ነው። በዓለም ላይ ያሉ ሀገራት በመጠባበቂያ ክምችት ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው የአሜሪካ ዶላር ይይዛሉ። ከፍተኛውን የዓለም አቀፍ ንግዳቸውን በዶላር ያካሂዳሉ። የቻይና የሕንድና የሌሎች በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ኢኮኖሚ በፍጥነት እያደገ ሲመጣ ግን ከዶላር ጥገኝነት ነፃ መሆን የግድ እየሆነ መጣ።

የጂኦፖለቲካል ጉዳይ ሌላው ምክንያት ነው። ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር ባለው የፖለቲካ ውጥረት ወይም የአሜሪካ ማዕቀብ ሊያስከትል በሚችል ስጋት ምክንያት ሀገራት በዶላር ላይ ያላቸውን ጥገኝነት መቀነስ ይፈልጋሉ። ሌላው በዶላር ላይ በእጅጉ መመካት ሀገሮችን ለወጪ ምንዛሪ ስጋት እና ለአሜሪካ ፌዴራል ሪዘርቭ ፖሊሲዎች ባርነት ያጋልጣል። የመጠባበቂያ ክምችት እና የንግድ ልውውጥ በሌሎች ገንዘቦች ማድረግ ግን ይህንን አደጋ ሊቀንስ ይችላል።

እንዲሁም የገንዘብ ሉዓላዊነት ፍላጎት ተጨማሪ መግፍኤ ነው። ሀገሮች በገንዘብ ፖሊሲያቸው ላይ የበለጠ ባለመብት ለመሆን፣ ነፃ የገንዘብ ፖሊሲ እንዲኖራቸው እና አሜሪካ በኢኮኖሚያቸው ላይ የምታሳድረውን ተጽዕኖ ለመቀነስ ከዶላር ውጭ ለመገበያየት እየወሰኑ ይገኛል። ሀገራችን ይሄን ይበል የሚያስብል ርምጃ ሰሞኑን ከተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ጋር አሀዱ ብላ ጀምራለች።

ኢትዮጵያና የተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ በራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት የሚያስችል የሁለትዮሽ የገንዘብ ልውውጥ(Currency Swap) ስምምነት ያደረጉ ሲሆን፤ ባለፈው ማክሰኞ ሐምሌ 9 ቀን 2016 ዓ.ም በተደረገው በገንዘብ ልውውጥ ስምምነቱ መሠረት፣ ኢትዮጵያ 46 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ የንግድና ኢንቨስትመንት ሥራን ያለ ዶላር አስፈላጊነት ከተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ ጋር መገበያየት ወይም መለዋወጥ ያስችላታል። ይህም ዋጋ ከሦስት ቢሊዮን ድርሃም ወይም 800 ሚሊዮን ዶላር ጋር ተመጣጣኝ ነው።

የገንዘብ ልውውጥ ስምምነት ማለት ዋጋቸው እኩል የሆኑ ምርቶችን መለዋወጥ (In Kind Trade) ሲሆን፣ ከምርቶቹ ዋጋ በላይ የሆነውን ትርፍ ዋጋ ብቻ በገንዘብ ያወራርዳሉ። ይህም ማለት ኢትዮጵያ ከዱባይ በብር መግዛት የምትችል ሲሆን፣ የተባበሩት ዓረብ ኤምሬቶችም በድርሃም ከኢትዮጵያ መግዛት ትችላለች።

በተጨማሪ ኢትዮጵያ ለምሳሌ ለተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ ላቀረበችው ዕቃ ክፍያውን በድርሃም ከተቀበለች ወይም የክፍያው ትርፍ ወደ ኢትዮጵያ ሆኖ በብር ለተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ ከከፈለች፣ ሁለቱ ሀገሮች ገንዘቦቹን ከሚጠቀሙ ሌሎች ሀገሮች ጋር እንዲገበያዩበት ያስችላል።

እንዲህ ዓይነት ስምምነት የብሪክስ (BRICS) ሀገሮች በተለይ በብዛት እየጀመሩት ሲሆን፣ ይህም በዋናነት ዶላር እንዲዳከም ለማድረግ ያለመ ነው። ኢትዮጵያና የተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ በቅርቡ የብሪክስ አባል ሀገሮች ሲሆኑ፣ ይህም ስምምነት የዚሁ አካል ነው ሲሉ ተንታኞች ይገልጻሉ። በተለይ አሜሪካ በብዙ ሀገሮች ላይ የምትጥለው ማዕቀብ ተፅዕኖ እንዳያርፍባቸው ብዙ ታዳጊ ሀገሮች ዶላርን ላለመጠቀም እየወሰኑ ነው። ቻይና፣ ሩሲያ፣ እንዲሁም ህንድ በብሪክስ ሥር ተመሳሳይ ስምምነት በማድረግ ያለ ዶላር በየራሳቸው ገንዘቦች መነገድ ከጀመሩ ሰንብተዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምሕረቱና የተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ካሊድ መሐመድ በፊርማቸው የደረሱበት ስምምነት ይህንኑ ያጠናክራል እየተባለ ነው። ሁለተኛው የመግባቢያ ስምምነት የሁለቱ ሀገሮች የንግድና ኢንቨስትመንት፣ እንዲሁም ማናቸውም ሸያጮች በራሳቸው ገንዘቦች እንዲደረጉ ያስችላል። ለዚህም የሁለቱ ሀገሮች የንግድ ባንኮች እንዴት የክፍያ ሥርዓቶቻቸውን ማቀላጠፍና የጽሑፍ መልዕክቶችን መላላክ እንደሚችሉ ያትታል።

> **በተናጥል በሚያደርጉት የክፍያ ስምምነት ለተለያዩ ሀገራት የተለያዩ የገንዘብ ዓይነት ይጠቀማሉ በየራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት ከወሰኑት ሀገራት ጋር በየራሳቸው ገንዘብ ነገር ግን ስምምነት ካልፈጠሩባቸው ሀገራት ጋር በተመረጡ የምንዛሬ ዓይነቶች ሊገበያዩ ይችላሉ**

‹‹ስምምነቱ ሁለቱ ሀገሮች በየራሳቸው ገንዘቦች ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲያካሂዱ ያስችላል። የኤሌክትሮኒክ ክፍያ ሥርዓቶቻችንም እንዴት ተዋህደው ሊሠሩ እንደሚችሉ ከስምምነት ደርሰናል። ይህ ስምምነት ሁለቱ ሀገሮች የጋራ ፍላጎቶቻቸውን ከግብ ለማድረስ ጠቃሚ ነው፤›› ሲሉ አቶ ማሞ ተናግረዋል። የኤምሬትስ ብሔራዊ ባንክ ገዥ በበኩላቸው ኢትዮጵያ ከዓረብ ኤምሬትስ የምገዛቸው ምርቶች በርካታ መሆናቸውን ገልጸው፣ በተለይ ደግሞ የኤምሬትስ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ በብዛት እንዲመጡ እንደሚያደርግ አስረድተዋል።

አቶ ዋሲሁን በላይ የተባሉ የኢኮኖሚ ባለሙያና ተንታኝ “The Ethiopian Economist View” በሚለው የቴሌግራም ገጻቸው የገንዘብ ልውውጥን በተመለከተ ሰፊ ትንታኔ አቅርበዋል። የዓለም አቀፍ ሁኔታ የኃይል ሚዛን ፍላጎት መቀያየር እና የአሜሪካ እና የአጋሮቿ ተደጋጋሚ የኢኮኖሚ እና የፋይናንስ ማዕቀብ በርካታ የዓለም ሀገራት በተለይ በፍጥነት እያደጉ ያሉት ሀገራት ዶላርን በሀገራቱ መካከል እንደ ማዕከላዊ የመገበያያ ገንዘብነት የመምረጣቸው ፍላጎት እየቀነሰ ነው።

ስለዚህ በርካታ ሀገራት ከሌሎች ሀገራት ጋር የሚኖራቸው የንግድ ግንኙነት ዶላር ላይ ያለውን ጥገኝነት በመቀነስ ወደ አማራጭ የክፍያ ስልቶችን መፈለግ ጀምረዋል። በተለይ ሀገራት ከንግድ አጋሮቻቸው ጋር በሚያደርጉት ስምምነት የንግድ እና የኢንቨስትመንት ክፍያዎቻቸውን በየራሳቸው ገንዘብ ለማድረግ (Bilateral Currency Swap Lines) በየማዕከላዊ ባንኮቻቸው በኩል ስምምነት እየፈጸሙ ነው። የዚህ ዋነኛ አቀንቃኞች ቻይና፤ ራሺያ እና ህንድ ሲሆኑ ብዙ ሀገራት እየተቀላቀሉት ነው።

በተናጥል በሚያደርጉት የክፍያ ስምምነት ለተለያዩ ሀገራት የተለያያ የገንዘብ ዓይነት ይጠቀማሉ በየራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት ከወሰኑት ሀገራት ጋር በየራሳቸው ገንዘብ ነገር ግን ስምምነት ካልፈጠሩባቸው ሀገራት ጋር በተመረጡ የምንዛሬ ዓይነቶች ሊገበያዩ ይችላሉ።

1.ቻይና ከንግድ አጋሮቿ ጋር በየራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት Network of Bilateral Currency Swap Agreements ቀዳሚዋ እና ትልቋ ሀገር ናት። የቻይና ማዕከላዊ ባንክ People’s Bank of China ከ41 የተለያዩ ሀገራት ብሔራዊ ባንኮች ጋር ስምምነት አድርጓል። ይህም ከ3.5 ትሪሊየን ዩሃን ወይም ከ480 ቢሊየን ዶላር በላይ አቻ ነው። ቻይና ከአሜሪካ ዶላር ቀጥሎ ከፍተኛ የዓለም አቀፍ የንግድ ግንኙነት ገቢ ያገኘችው ስምምነት ካደረገችባቸው ሀገራት ነው።

በIMF ጥናት ከቻይና ጋር ስምምነት ያደረጉ ሀገራት የክፍያ መጠናቸው በ2014 ከነበረበት ዜሮ ከመቶ በ2021 ድርሻው 20በመቶ ደርሷል። የተወሰኑ ሀገራት ከቻይና በቻይና ገንዘብ መገበያየት ከመቻላቸው በተጨማሪ ከሌላ ሶስተኛ ሀገር የቻይናን ገንዘብ ተጠቅመው ክፍያ መፈጸም ይችላሉ። ለምሳሌ ህንድ ከራሽያ በቻይና ገንዘብ ነዳጅ ትሸምታለች። ቻይና፤ ሆንግ ኮንግ፤ ታይላንድ እና የተባበሩት አረብ ኤሜሬትስ በማዕከላዊ ባንኮቻቸው በኩል የራሳቸው ዲጂታል የክፍያ ዘዴ ፈጥረው ግብይት ለመለዋወጥ ሥራ ጀምረዋል (mBridge)።

2. ህንድ ስምምነት ከምታደርግባቸው ሀገራት ጋር በራሷ ገንዘብ (ሩፒ) ለመገበያየት ወስናለች። እስካሁን ከ22 ሀገራት ጋር ስምምነት ደርሳለች። ህንድ የዛሬ ዓመት ከተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ጋር በሩፒ ለመገበያየት ስምምነት አድርጋለች። በርግጥ ህንድ ከመካከለኛው ሀገራት ጋር በሩፒ የመገበያየት ነባር ልምድ ነበራት። ኢራን እና ማይናማር ተመሳሳይ ፍላጎት አላቸው።

ምን ማለት ነው? ስምምነት ያደረጉ ሀገራት በህንድ ባንኮች አካውንት ከፍተው ወይም Special Vostro Rupee Accounts ሩፒ ይቆጥባሉ። ከዚያ ለሚያደርጉት ሸመታ ክፍያ ከአካውንታቸው ይፈጽማሉ። በተመሳሳይ የህንድ ድርጅቶች ስምምነት ባለባቸው ሀገራት ሂሳብ ከፍተው የየሀገራቱን ገንዘብ ይቆጥባሉ ለሸመታቸው ክፍያ ይፈጽማሉ ማለት ነው። ህንድ በዓለም አቀፉ ንግድ ውስጥ ያላት ድርሻ ከ1.8 በመቶ ባይበልጥም በቻይና ከሚመራው የ15 በመቶ ንግድ ጋር ሲደመር ተጽዕኖው ቀላል አይደለም።

3.ራሺያ በተደጋጋሚ የማዕቀብ ሰለባ በመሆኗ የቻይናን ገንዘብ መገበያያ አድርጎ ወደ መቀበል አዘንብላለች። በተለይ ከ2022 ጀምሮ ከዩክሬን ጋር ጦርነት ውስጥ መግባቷን ተከትሎ በውጭ ሀገራት የነበሯት የመጠባበቂያ አካውንቶች መዘጋት እና ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ዝውውር ዘዴ SWIFT መታገዷ በሀገራት ጋር በተናጥል ገንዘቦች ለመገበያየት ገፊ ምክንያት ሆኗታል። ራሺያ ከቻይና ጋር ሁለት ሶስተኛ የሚሆነውን የንግድ ልውውጥ እያከናወነች ያለችው በሩብል እና በዩሃን ነው።

ራሺያ ከ2022 አጋማሽ ጀምሮ የራሺያ ወዳጅ ያልሆኑ ሀገራት ነዳጅ ከራሺያ ለመሸመት የራሺያ ገንዘብ ማለትም ሩብል ይዘው መገኘት አለባቸው የሚል ውሳኔ አውጥታለች። ለምሳሌ እንግሊዝ ከራሺያ ነዳጅ ለመግዛት ብትፈልግ መክፈል ያለባት በፓውንድ፤ በዩሮ ወይም በዶላር ሳይሆን በሩብል ነው። ከዚህ ውሳኔ በኋላ 54 የውጭ ሀገር ድርጅቶች ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ዝውውር ዘዴ SWIFT ቁጥጥር ውጭ የሆነ Gazprombank የሚባል አካውንት ከፍተው ሩብል በመቆጠብ ይጠቀማሉ።

የእስያ ሀገራት የሆኑት ኢንዶኒዢያ፤ ማልይዥያ፤ ሲንጋፖር እና ታይላንድ (ፊሊፒንስ ትቀላቀላለች ተብሎ ይጠበቃል) እርስ በርስ በየራሳቸው ገንዘብ ለመገበያት ስምምነት አድርገዋል። ስምምነቱ Local Currency Settlement Framework ይባላል። የብሪክስ አባል ሀገራት በየራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት (BRICS Pay) ስምምነት ያደረጉት የዛሬ ዓመት ነው። ኢትዮጲያ እና የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ በተጨማሪ የብሪክስ አባል ናቸው። ኢትዮጵያ እና የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ በየራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት ስምምነት አድርገዋል፤ ስምምነቶቹ የተፈረሙት በሁለቱ ሀገራት ማዕከላዊ ባንክ ገዢዎች ነው።

የወደፊት ስምምነቱ የክፍያ ሥርዓት (UAESWITCH እና ETHSWITCH ለማስተሳሰር) እና የክፍያ መረጃ የመለዋወጥ ዘዴዎችን የሚጨምር ነው። ነገር ግን በየራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት የወሰኑት Currency Swap የስምምቱ ማዕቀፍ የ3 ቢሊየን ድርሃም እና የ46 ቢሊየን ብር ዋጋ ያለው ነው። ምን ማለት ነው? የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ 3 ቢሊየን ድርሃም የምታስቀምጥ ሲሆን ኢትዮጵያም በተመሳሳይ በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ማዕከላዊ ባንክ 46 ቢሊየን ብር ታስቀምጣለች ማለት ነው።

ይህንን ያስቀመጡትን ገንዘብ እስኪጨርሱ የሁለቱ ሀገራት ብሔራዊ ባንኮች ከአካውንቶቻቸው ወጪ እያደረጉ ሸመታ እና ኢንቨስትመንት ያከናውናሉ ማለት ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ የመቶ ሚሊየን ብር ዋጋ ያለው መኪና ከተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ለመግዛት ብታስብ በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ማዕከላዊ ባንክ ካላት 46 ቢሊየን ብር አውጥታ ትገዛለች ማለት ነው። በተመሳሳይ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ከኢትዮጵያ የ100 ሚሊየን ድርሃም ዋጋ ያለው ቡና ለመግዛት ብትፈልግ በኢትዮጵያ ማዕከላዊ ባንክ ካላት 3 ቢሊየን ድርሃም ላይ አውጥታ ትገዛለች ማለት ነው። የዋጋ ተመኑ በገንዘቦቹ መካከል ባለው ልዩነት ይሆናል። አንድ ብር አንድ ድርሃም ይሆናል ማለት አይደለም።

በመጀመሪያ ስምምነታቸው ማለትም የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የምታስቀምጠው 3 ቢሊየን ድርሃም እና ኢትዮጵያም በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ማዕከላዊ ባንክ የምታስቀምጠው 46 ቢሊየን ብር እስኪያልቅ ነው። የሁለቱም ሀገራት ብሔራዊ ባንኮች ይህንን ያስቀመጡትን ገንዘብ ለየትኞቹ ዘርፎች እና ምርቶች እንደሚውል እና በምን ያህል ጊዜ እየተጠቀሙ እንደሚጨርሱት በቀጣይ የሚወስኑ ይሆናል። የዚህ ዓይነቱ ስምምነት በጥምረት የሚሰሩ የንግድ አጋርነት ለመፍጠር እና የንግድ ልውውጥ መጠንን ለማስፋት ጠቀሜታ ይኖረዋል፤ የግብይት ወጪን ይቀንሳል፤ ከሶስተኛ ሀገር ማዕቀብ ነፃ ነው።

ሻሎም ! አሜን ።

# ወቅታዊ

# «ማሻሻያው የገንዘብን አቅም የሚያዳክም አይደለም»

- አቶ በረከት ፍስሃፅዮን

በፕላንና ልማት ሚኒስቴር የልማት እቅድና የመንግሥት ኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥራ ክፍል ዋና ሥራ አስፈጻሚ

ራስወርቅ ሙሉጌታ

በቅርቡ ተግባራዊ መደረግ የጀመረው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ በብዙዎች ዘንድ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኗል። መንግሥት ያካሄደውን አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተከትሎ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ያወጣው ብሔራዊ ባንክ በበኩሉ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ዘርፈ ሁሉን አቀፍ ጠቀሜታዎች እንዳሉት በመግለጫው አስታውቋል።

ከእነዚህ መካከል የሀገሪቱን የዕድገት ደረጃ እና ከቀሪው ዓለም ጋር ያላትን እያደገ የመጣ ትስስር የሚያጠናክር መሆኑ በዋነኛነት ተጠቅሷል። የጥቁር ገበያ መስፋፋትን የሚቀንስ፤ ከፍተኛ የዋጋ ንረትን በዘላቂነት ለመቆጣጠር የሚያስችል፤ በከበሩ ማዕድናት የሚደረግ ሰፊ የኮንትሮባንድ ንግድን የሚያስቀር፤ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ከባንክ ሥርዓት ውጭ ከሀገር እንዳይሸሽ የሚያደርግ መሆኑም ተጠቁሟል። የውጭ ኢንቨስተሮችን በመሳብ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን የሚያሳድግ መሆኑም ተጠቅሷል። በርግጥ ይህ ማሻሻያ እነዚህን ሁሉ ትሩፋቶች ይዟል ? ስንል በፕላንና ልማት ሚንስቴር የልማት እቅድና የመንግሥት ኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥራ ክፍል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከሆኑት ከአቶ በረከት ፍስሃፅዮንን አነጋግረን የሚከተለውን ይዘን ቀርበናል።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይፋ የተደረገው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ዋና አላማ ምንድን ነው ?**

**አቶ በረከት፡-** የአሁንን ማሻሻያ ለማየት ከዚህ በፊት የነበሩትንም የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች መለስ ብሎ መቃኘት ይጠበቃል። ከዚህ በፊት ቀደም ብለው የነበሩ የማክሮ ኢኮኖሚ ሥርዓቶች ከፍተኛ መዛባቶችንና ስብራቶች የነበሩባቸው ናቸው። በዚህም የተነሳ ኢኮኖሚው ያጋጠሙትን መዋቅራዊ ችግሮች ለመፍታት በርካታ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎች ተግባራዊ ሲደረጉ ቆይተዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአስር ዓመት የልማት እቅድና የመጀመሪያው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተግባራዊ መደረጉ ይታወሳል። በዛ ውስጥ በዋነኝነት የተለዩ የማክሮ ኢኮኖሚ ጉዳዮች የዘርፍ ምርትና ምርታማነትን የሚመለከቱና የኢንቨስትመንት ከባቢያዊ ሁኔታን ማሻሻልን የሚመለከቱት ነበሩ።

በወቅቱም በቀዳሚነት ትኩረት ተሰጥቷቸው የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርሙ ከያዛቸው ጉዳዮች መካካል በፊሲካል ሪፎርም የመንግሥትን የእዳ ጫና መቀነስ አንደኛው ነው። የመንግሥት ገቢ አስተዳደር ውጤታማ ማድረግ፤ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ውጤታማነት ማረጋገጥ፤ በገንዘብ ፖሊሲ ውስጥም ወደ ዘመናዊ የገንዘብ ፖሊሲ ሽግግር ማድረግ የሚሉት ናቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ የውጭ ምንዛሬ ተመን ውጤታማ እንዲሆን በኢኮኖሚው ውስጥ ያሉ መዛባቶችን ማረም የሚባሉት ተጠቃሾች ናቸው።

ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው እነዚህን ሰፊ ጉዳዮችና ብዙ ዘርፎችን ያካተተ ሲሆን፤ አብዛኞቹን መተግበር የተቻለ ሲሆን አመርቂ ውጤትም ተመዝግቦባቸዋል። ከእነዚህ ውስጥ በዋነኝነት በተለያዩ ምክንያቶች ያልተከናወነው የውጭ ምንዛሬ ተመንን የተመለከተው ጉዳይ ብቻ ነበር። በአንጻሩ ዋነኛ ማነቆዎችን ለመፍታት መከናወን የነበረበት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ አካል ነበር።

በመሆኑም አንደኛው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርም ሲጠናቀቅ ተከናውነው ውጤታማ የሆኑትን አጠናክሮ ለመቀጠል ያልተከናወኑትን ለመሥራት ትልቅ ድርሻ ያለው ነው። በተጨማሪም በኢኮኖሚ ውስጥ ያሉ መዛባቶችን ለመፍታት መወሰድ ካለባቸው ማሻሻያዎች መካከል አንዱ ከውጭ ምንዛሬ ጋር በተያያዘ ያለው የአሠራር ክፍተት ነበር። በአጭሩ አሁን የተወሰደው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በድንገት የተከሰተ ሳይሆን ቀደም ብሎ ሲወሰዱ ከነበሩት ጋር የሚያያዝ እና በሁለተኛው ሀገር በቀል ሪፎርም ማሻሻያ ለመከወን ቀድሞ በእቅድ የተያዘም ነው።



ፎቶ፡- ገበበ ገብሬ

**እሁን በተወሰደው ርምጃ በገበያ ውስጥ የሚኖረው የውጪ ምንዛሬ ተመን በራሱ በገበያው የሚወሰን በመሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል ይሆናል**

በአጠቃላይም የአሁኑ ማሻሻያና ከዚህ በፊት የተከናወኑትም በኢትዮጵያ ዕድገትን ለማፋጠን፤ የዋጋ ንረትን ለማርገብ፤ የፊስካል አቅምን ለማሳደግ፤ የወጪ ንግድንና የውጭ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና የሀገሪቱን ዓለም አቀፍ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት ለማሳደግ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም ማሻሻያው ምን ምን ፋይዳዎችን ያስገኛል ተብሎ ይጠበቃል ?**

**አቶ በረከት፡-** ማሻሻያው በርካታ ጠቀሜታዎችን የሚያመጣ ነው። ከእነዚህም ውስጥ አንኳር የሆኑትን ብናነሳ የመንግሥትን የእዳ ጫና ለማቃለል ይረዳል። በገበያ ውስጥ የውጪ ምንዛሬ ሥርጭትን ፍትሃዊና ውጤታማ ለሆኑ ዘርፎች ብቻ እንዲውሉ ለማድረግ ያግዛል። በእዚህም በኢኮኖሚው የተሻለ አስተዋጽኦ ያላቸው ዘርፎች የተሻለ የውጪ ምንዛሬ እንዲያገኙ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ይጠቅማል። በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ አጠቃላይ የውጪ ምንዛሬ ዋጋን በማስተካከል የኢኮኖሚ ተወዳዳሪነትን ያጎለብታል። ይህንንም ተከትሎ የወጪ ምርትን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማድረግ የወጪ ንግድ ገቢን ያሳድጋል። በአንጻሩ ከውጪ የሚገቡ ውጤታማ ያልሆኑ የፍጆታ ምርቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ያደርጋል። በዚህ ሰንሰለት ውስጥ የሚኖሩትን የኢኮኖሚ ተዋናዮች በሙሉ ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ ይሆናል።

ከዚህም ባለፈ ሪፎርሙ አጠቃላይ እንደመሆኑ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን የማሳደግ አቅም ይኖረዋል። በሀገር ውስጥ አቅም ሊተኩ የሚችሉ ምርቶችን ለማምረትም ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ሰፊ እድል የሚከፍት በመሆኑ ለበርካቶች የሥራ እድል የሚፈጠር ይሆናል። እንደ ሀገር ገበያንና ውድድርን መሠረት ያደረገ የተረጋጋ ኢኮኖሚ እንዲፈጠርም የሚጠቅም ይሆናል። ትክክለኛውን ዋጋ ይዞ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን በማረጋገጥ ከአቅም ጋር የተመጣጠነ የወጪና የገቢ ንግድ እንዲኖር ያደርጋል። ተወዳዳሪ መሆን መቻል ደግሞ የማክሮ ኢኮኖሚ ስብራቶችን ለመጠገን የሚጠቅም ይሆናል።

ይህም የንግድ ሚዛን ጉድለትን ለመፍታትና የክፍያ ሚዛንን ለማስተካከል ትልቁን ድርሻ ይወስዳል። በጥቅሉ በግሉ ዘርፍ ላይ የተመሠረተ ጠንካራ ነፃ ኢኮኖሚ ዋናው ማረጋገጫው በገበያ የተመሠረተ ዋጋ መኖር ነው። በገበያ ውስጥ የተለያዩ ዋጋዎች አሉ። የነገረ ምርት ገበያ፤ የሸቀጥ ገበያ፣ የውጪ ምንዛሬ ገበያ እና የፋይናንስ ዘርፍ ገበያ ተብለው ይለያሉ። በዚህ ሂደት ሁሉ ማሻሻያው ዋጋ በፍላጎትና አቅርቦት የሚወሰን ሆኖ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- የመንግሥትን የእዳ ጫና እንደሚቀንስ አንስተዋል ይህ በምን መልኩ ሲሆን ይችላል ?**

**አቶ በረከት፡-** የእዳ ጫና የሚባለው ከዚህ በፊት የነበሩትንና በቀጣይ ኢኮኖሚው የሚፈልጋቸውን የልማት ፋይናንስ ፍላጎት የሚያካትት ነው። በማሻሻያ ውስጥ እንደተቀመጠው የእዳ ሽግሽግ ማለትም እዳ በዘላቂነት ከመፍታት አንጻር የተደረጉ ስምምነቶች አሉ። ይህም እዳውን በማሸጋሸግ የሚከፈልበት ጊዜ እንዲዘገይ ያደርጋል። ይህ አሁን ያለውን ጫና የሚያረግብ ሲሆን፤ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ተወዳዳሪነትን በማሳደግ የወጪ ንግድን የሚያበረታታና የንግድ ሚዛኑን የሚያስተካክል ይሆናል። ይህም ኢኮኖሚውን በማሳደግ የመንግሥት ገቢን በመጨመር እዳ የመክፈል አቅም እንዲኖር ይረዳል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አበዳሪዎች ትክክለኛ ገበያ እንዳለ ካወቁ የሚያበድሩት ገንዘብ ሊመለስላቸው እንደሚችል ስለሚያምኑ ለሌሎች ጉዳዮች እና በተጨማሪነት ለልማት የሚውል ፋይናንስ ለማግኘትም የሚቻልበት እድልን የሚፈጠር ይሆናል። ይህ ሲባል ሁሌ በብድር እንኖራለን ማለት ግን አይደለም። የሚገኘውን ጥሪት በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል ብድር ለመክፈል መቻልና፤ ከዚህም አልፎ በመቆጠብም ሌሎች የልማት ተግባራትን በራስ አቅም ለማከናወን መደላድል ለመፍጠር ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ማሻሻያው ወደ ጎረቤት ሀገሮች የሚደረግ የኮንትሮባንድ ንግድን ለመቀነስ፤ ሳኪዎችና አስመጪዎች የሸቀጦችን ዋጋ ያለ አግባብ ከፍ ወይም ዝቅ እንዳያደርጉ የሚኖረው ጠቀሜታ እንዴት ይታያል።**

**አቶ በረከት፡-** በገበያ ውስጥ አንዱ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ነገር የውጪ ምንዛሬ ተመን ነው። የውጪ ምንዛሬ ተመን መወሰን ያለበት ደግሞ በመደበኛው የፋይናንስ ሥርዓት ብቻ ነው። ከዚህ ውጪ ከሆነ የውጪያዊ አካላት ጣልቃ ገብነት አለ ማለት ነው። ከዚህ ቀደም ከውጪ ምንዛሬ ጋር በተያያዘ የነበሩት ሥርዓቶች አምራቾችን የሚያበረታቱ አልነበሩም። በዚህም የተነሳ የውጪ ምንዛሬን በቀጥታ ለማግኘት ምርቶችን ወደ ውጭ ሀገራት በተለይም ወደ ጎረቤት ሀገራት አምራቾች በማውጣት የሚሸጡበት አካሄድ ነበር። በተጨማሪ ሲተገበር የነበረው የውጪ ምንዛሬ ሥርዓት ትክክለኛውን የገበያ የዋጋ ተመን የሚያመላክት ባለመሆኑ የተሻለ ለማግኘት አማራጭ የሚያማትሩትም በርካቶች ናቸው።

አሁን በተወሰደው ርምጃ በገበያ ውስጥ የሚኖረው የውጪ ምንዛሬ ተመን በራሱ በገበያው የሚወሰን በመሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል ይሆናል። በእዚህም የገንዘብ ምጣኔው ተመጣጣኝ የሆነና ተወዳዳሪነትን የሚያንጸባርቅ መሆን ይችላል። ይህም አምራቾች ያመረቷቸውን የማዕድንም ሆነ ሌሎች ምርቶች የተለየ ጥቅም ስለማያገኙ በሀገር ውስጥ ገበያ ለመሸጥ ይበረታታሉ።

እስካሁን በነበረው ልምድ በውጭ ምንዛሪ የሚካሄድ ኢ-መደበኛ ገበያ እየተስፋፋ በመምጣቱ አብዛኛው የንግድ ማህበረሰብና የህዋላ ተገልጋዮች በአብዛኛው በጥቁር ገበያ ሲገዙና ሲሸጡ ይስተዋላል። አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያ ይህንን የገበያ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባና እንዲህ ዓይነቱን ኢ-መደበኛ አሠራር በማስቀረት ተወዳዳሪ፣ ግልጽና አመቺ ወደሆነ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት መግባትን የሚያበረታታ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- በማሻሻያው ለኑሮ ውድነት መደጎሚያ መንግሥት ከውጭ የሚገቡ የአንዳንድ መሠረታዊ ሸቀጦችን ዋጋ በጊዜያዊነት ለመደጎም ወስኗል። ነገር ግን ማሻሻያው ህብረተሰቡን በዘላቂነት ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር ምን ጥቅም**

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# «ማሻሻያው የገንዘብን አቅም...

ከገጽ 7 የዞረ

**ይኖራቸዋል?**

**አቶ በረከት፡-** በመሠረቱ ማሻሻያው ሲደረግ ጥልቅ በመሆኑ ተጽእኖ ይደርስባቸዋል ተብለው የታሰቡ የማህበረሰብ ክፍሎችን ለመታደግ ብዙ ተሰርቷል። የድርድሩም አካል ሆኖ ዝግጅት ተደርጎበታል። በዚህም ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞችን ተደራሽ የማድረግ፤ መሠረታዊ የሆኑ እንደ ነዳጅ፤ ማዳበሪያ፤ ዘይት መድኃኒት ያሉ ምርቶች ድጎማ የሚደረግባቸው ይሆናል። ለእዚህ የሚሆን በቂ ፋይናንስም የተዘጋጀ ሲሆን፤ በተጨማሪ መንግሥት የገቢ አቅምን በማሳደግ ተጽእኖ የሚደርስባቸውን ዜጎች ለመታደግ በየወቅቱ የሚሰራቸው በርካታ ሥራዎች ይኖራሉ። ይህም ማሻሻያውን ተከትሎ በገበያ ውስጥ የሚፈጠረውን የዋጋ ንረት ለመቆጣጠር የሚያስችል ይሆናል።

ይህም ሆኖ እንዲህ ዓይነት ትልልቅ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ሲወሰዱ በገበያ ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮች እንደሚኖሩ ይጠበቃል። ለእዚህም በመንግሥት በኩል ማህበረሰቡ ለችግር እንዳይጋለጥ መሠረታዊ በሚባሉ ሸቀጦች ላይ የሚወሰዱ ተከታታይነት ያላቸው ቁጥጥሮችና ርምጃዎችም ይኖራሉ። በተለይም ከጉዳዩ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የማይኖራቸው የዋጋ ጭማሪዎች ላይ ጥብቅ ክትትል የሚደረግ ይሆናል።

ማሻሻያው የተደረገው እንደ ከዚህ ቀደሙ የውጪ ምንዛሬ መጠንን ማዳከም ሳይሆን፤ ገበያን መሠረት ያደረገ የውጪ ምንዛሬ ተመን ሥርዓት መዘርጋት ነው። ይህም ማለት መንግሥት ዋጋ የሚተምንበት ሳይሆን ባንኮችና ደንበኞች በሚኖራቸው ግንኙነት የሚፈጠር የዋጋ ተመን ይኖራል ማለት ነው። ይህም ከነበረው ከተለመደው አካሄድ የተለየ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። በዚህም ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በተወሰነ ደረጃ የዋጋ ጭማሪ ሊያሳዩ ይችላሉ።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከውጭ የሚገቡትን ምርቶች ምንነት ተለይቶ መታየት አለበት። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ከከተሞች ውጭ የሚኖር ነው። የፍጆታው ዓይነትም በቀዳሚነት ራሱ የሚያመርታቸው ሲሆኑ፤ አንዳንድ በግብዓትነት የሚጠቀምባቸውም በስትራቴጂ የተያዙት ናቸው። በመሆኑም ይከሰታል ተብሎ የሚጠበቀው ጭማሪ አብዛኛውን ዜጋ ለተጋነነ ችግር የሚያጋልጥ አይሆንም። ከዚህም በተጨማሪ አብዛኛው ሕዝብ እንደ ትምህርት ጤና ያሉ መሠረታዊ ነገሮችን በነፃ ተጠቃሚ መሆኑ ማሻሻያውን ተከትሎ ለሚፈጠር ለውጥ የመጋለጥ እድሉም ዝቅተኛ ነው። ይህም ሆኖ አብዛኛውን ሕዝብ የሚነኩ ጉዳዮችና ያንን ተከትሎ የሚከሰቱ ነገሮችን ለመቆጣጠር ዝግጅት ተደርጓል። በአንጻሩ ይፈጠራል ተብሎ የተሰጋው የአንዳንድ ምርቶች ዋጋ መጨመር የሀገር ውስጥ አምራቾችን የሚያበረታታ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- በሀገሪቱ እየተከናወኑ ያሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች በማስቀጠል ረገድ የሚኖረው ጠቀሜታ ምንድን ነው?**

**አቶ በረከት፡-** ከዚህ ቀደም ኢኮኖሚውን አንቀው የያዙ የውጪ ምንዛሬ አሠራር ሥርዓት ነበር። ይህንን አዲሱ ማሻሻያ በመሻገር ውጤታማ ለሆኑና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለሚኮንባቸው ዘርፎች ተደራሽ ለማድረግ ያስችላል። ይህም ለሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ነው። እዚህ ላይ የውጭ ኢንቨስተሮች ወደ ሀገር ሲገቡ ይዘዋቸው የሚመጡ እድሎችና መልካም አጋጣሚዎችም እንዳሉ መታወቅ አለበት። ኢንቨስትመንቱ አጠቃለይ ይነቃቃል። የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ውጤቶችን በግብዓትነት የሚጠቀሙም ይኖራሉ። ያለውን አቅም በአግባቡ በመጠቀም የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት ሂደትን የሚያበረታታም ይሆናል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ውጤታማ የሆኑ ባለ ሀብቶች ተጠቃሚ የሚሆኑ ሲሆን፤ ከእነዚህ በፊትም ውጤታማ የሆነው አሠራር ውስጥ ያልነበሩ የሚገጥማቸው ችግር ሊኖር ይችላል። ነገር ግን ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ የሀገሪቱ የመሠረተ ልማትና ማህበራዊ ኢንቨስትመንት ጥራቱና ውጤታማነትን እንደጠበቀ እየተስተካከለ የሚቀጥል መሆኑ ነው።

በዚህ ሂደት የመንግሥት አቅም እየተጠናከረ ይመጣል። ይህንንም ተከትሎ የኢኮኖሚ እድገት ለማስቀጠል የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የመንግሥት የማህበራዊና የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚቀጥሉ ይሆናል። ለዚህም በሪፎርሙ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ የሚደረግ ከፍተኛ መጠን የሚኖረው ፋይናንስ ይኖራል። ይህም አሁን ቃል ከተገባው ባለፈ ይህንን ስምምነት እየጠበቁ ካሉ ሌሎች አካላት የሚገኝ ነው። በመንግሥት በኩልም ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ሌሎች ምንጮች የሚያገኛቸውን ገቢዎች ለማሳደግ የሚሰሩ ጠንካራ ሥራዎች ይኖራሉ። በተጨማሪ የመንግሥት ወጪ በአግባቡ ተመርቶ ውጤታማ እንዲሆን በመንግሥት ወጪ አስተዳደር ላይም የሚወሰዱ ተከታታይነት ያላቸው ርምጃዎችም ይኖራሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ማሻሻያ የብሔራዊ ባንክን ሚና የሚገዳደር አይሆንም ?**

**አቶ በረከት፡-** የገበያው ዋጋ በባንኮችና በደንበኞች የሚወሰን ሲሆን የብሔራዊ ባንክ ሚና የሚኖረው ዋጋን የማረጋጋት ተግባር ብቻ ነው። ይህም የሚሆነው አንደኛ ከቁጥጥር ውጪ የሆኑ አለመረጋጋቶች ቢከሰቱ ካለው መጠባበቂያ በቂ የውጪ ምንዛሬ ወደ ገበያው በማስገባት እጥረቱን የሚታደግ ይሆናል። በተጨማሪ ኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖሩ መጋጋልና መቀዛቀዞችን ለማስተካከል በተዘዋዋሪ የገንዘብ ፖሊሲ አማካይነት የሚወስዳቸው የተለያዩ ርምጃዎችም ይኖራሉ። እነዚህም የተረጋጋ የኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታ በመፍጠር ትክክለኛ የዋጋ ተመን እንዲኖር የሚያስችሉ ይሆናል።

እንደ አጠቃላይ በውጭ ምንዛሪ ተመን ወይም በአገልግሎት ክፍያ ረገድ የማጭበርበር ድርጊት መፈጸም በጥብቅ የተከለከለ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተለያዩ ዘዴዎችን፣ በተለይም የቴክኖሎጂ ውጤቶችን፣ በመጠቀምና እንደ አስፈላጊነቱ ከፋይናንስ ደህንነትና ሌሎች ሕግ አስከባሪ አካላት ጋር በመተባበር እነዚህን የቁጥጥርና የክትትል ሥራዎች ያከናውናል። ሕግን በሚተላለፉት ላይም አስተማሪ ርምጃ የሚወስድ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ማሻሻያው በውጭ አካላት ተጽእና የተደረገ ስለመሆኑ ይነገራል። ለዚህም ማሻሻያውን ተከትሎ ከአንዳንድ አበዳሪዎች እየተደረጉ ያሉ ድጋፍና ማበረታቻዎች ማሳያ ናቸው የሚል አሉ። ይህን እንዴት ያዩታል ?**



> **ይመጣሉ የተባሉት ተጽእኖዎች በአንዳንድ አካላት እንደሚገለጹት የተጋነኑ አይደሉም:: ሊከሰቱ የሚችሉት ጉዳዮች ቀድመው የተለዩና ቅድመ ዝግጅትም የተደረገባቸው ናቸው**

**የተደረገውስ ማሻሻያ ወቅቱን የጠበቀ ነው?**

**አቶ በረከት፡-** ሪፎርሙ የመጣው አጠቃላይ ሁሉን አቀፍ ሆኖ ነው። በሀገር በቀል ማሻሻያ «አንድ» ላይ የተጀመሩ በርካታ ሥራዎች ነበሩ። በሀገር በቀል ማሻሻያ «ሁለት» በእቅድ የተቀመጡ አሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ኢኮኖሚው ያለበትን ውስንነት ለመፍታት መወሰድ ካለባቸው ርምጃዎች መካከል አንዱ ይኸው ማሻሻያ ነው። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ስትጠቀምበት የነበረው የውጪ ምንዛሬ ዓይነት ሥርዓት ያላቸው ሀገራት በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። በዓለም ላይ በአብዛኛው እየተተገበረ ያለውና ውጤታማ የሆነው አሁን በሀገራችን ወደ ትግበራ የገባው በገበያ ላይ የተመሠረተ የውጪ ምንዛሬ ሥርዓት ነው። በመሆኑም ይህ ርምጃ ዘግይቷል ሊባል ይችላል፤ እንጂ ጊዜው አይደለም ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የለም።

የውጪ ተጽእኖን በተመለከተም የተነሳው ሃሳብ ስህተት ነው። በዚህ ረገድ መታወቅ ያለበት ጉዳይ አለ። ድርድሩ ረጅም ጊዜ የወሰደ ነው። ይህም ሊሆን የቻለው የዜጎችንና የሀገሪቱን ጥቅም ለማስጠበቅ ብዙ መፈተሽ የነበረባቸው ጉዳዮች ስለነበሩ እነሱን ለማጽዳት ነው። ለምሳሌ የሀገርን ጥቅም ለማስጠበቅ አሁንም ወደ ውጪ የሚሄድ የካፒታል አካውንት በነበረበት እንዲቀጥል ተደርጓል። ይህ የተደረገው ከማሻሻያው ጋር ተያይዞ የውጪ ምንዛሬ ልውውጥ ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽእኖ ከግምት በማስገባት የሀገር ጥቅምን በማስቀደም ነው።

በርግጥ በሪፎርሙ የተካተቱት ጉዳዮች ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ያልተለመዱ ናቸው። ይህም ሆኖ ሊደርሱ የሚችሉ ተጽእኖዎችን ለመፍታት በሚያስችል ሁኔታ የተዘጋጁ ናቸው። መንግሥት ከለውጡ በፊት ከፍተኛ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባቶች ገጥመውት እንደነበር ይታወሳል። አሁን ላይ ግን በተለይም የእዳ ጫናውን በተወሰነ መልኩ ማቅለል ቢቻልም፤ አሁንም ያለው ቀላል የሚባል አይደለም። እነዚህ ተግዳሮቶች ለመሻገር በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፍ የሚጠይቅ ይሆናል። ድርድሩ በጥንቃቄ በከፍተኛ ባለሙያዎች እንዲከናወን የተደረገው ለዚህም ነው። ባጠቃላይም ድርድሩ የሀገራችንን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚያስችል መልኩ የተከናወነ ነው ለማለት ይቻላል። በውጤቱም በኢኮኖሚው ውስጥ ያሉ ስብራቶችን ለመጠገን የሚያስችል ይሆናል። በተጨማሪም የአሁኑ ጅምር በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ የፋይናንስ ተቋማት ጋር ያለው ግንኙነት አጠናክሮ ለማስቀጠልም የሚያግዝ ይሆናል። በዚህ ረገድ ኢኮኖሚው እያደገና መዋቅራዊ ችግሮች እየተፈቱ ሲሄዱ፤ ተሳትፏችንም የሚጨምር በመሆኑ የመደራደር አቅማችንም ይጎለብታል።

**አዲስ ዘመን፡- የተደረገው ማሻሻያ የገንዘብን አቅም የማዳከም ርምጃ ነው ይባላል። ይህንን እንዴት ያዩታል?**

**አቶ በረከት፡-** ገንዘብን የማዳከም ርምጃ የሚባለው በዋነኝነት መንግሥት ከነበረው የውጪ ምንዛሬ ተመን ሥርዓት የተለየ ክፍያ የሀገር ውስጥ ገንዘብን በሚያዳክም መልክ የሚወስንበት ሥርዓት ሲዘረጋ ነው። ማለትም በገበያ ውስጥ አቅርቦትንና ፍላጎትን መሠረት ሳያደርግ መወሰን ነው። አሁን የተደረገው በገበያ ላይ የተመሠረተ የዋጋ ተመን ማሻሻያ ሥርዓት ግን መንግሥት ገበያውን ክፍት በማድረግ የመቆጣጠር ሥራ ብቻ እንዲያከናውን የሚያደርገው ይሆናል። ተመኑ የሚወሰነው ግን በገበያ ውስጥ ባለው የውጪ ምንዛሬ አቅርቦትና ፍላጎት መካከል በሚኖር ትስስር ይሆናል ማለት ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው በዚህ ሂደት ብሔራዊ ባንክ የሚኖረው የማረጋጋት ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት በቀጥታ ገብቶ የሚያስቀምጠው ተመን አይኖርም ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ማሻሻያውን ተከትሎ በህብረተሰቡ ዘንድ የተፈጠሩ ግርታዎችና መደናገሮች ለማስተካከል ምን ሲሰራ ታስባል።**

**አቶ በረከት፡-** ይመጣሉ የተባሉት ተጽእኖዎች በአንዳንድ አካላት እንደሚገለጹት የተጋነኑ አይደሉም። ሊከሰቱ የሚችሉት ጉዳዮች ቀድመው የተለዩና ቅድመ ዝግጅትም የተደረገባቸው ናቸው። የሚፈጠሩትን ተጽእኖዎች ለመከላከልም የሚወሰዱ ተከታታይ ርምጃዎች ይኖራሉ። በርግጥ ማሻሻያው ጥልቀት ያለውና መጠነ ሰፊ ጎዳዮችን የሚነካካም ነው። በአንጻሩ በርካታ መልካም እድሎችንም የያዘ ነው። በመሆኑም ስለማሻሻያው ለማወቅ የነበሩትንና ያሉትን በቀጣይም ሊከሰቱ የሚችሉትን ነገሮች በጥልቀት መረዳት ይጠበቃል። በመሆኑም ዜጎች መረጃዎችን ከተገቢው ምንጭ ይህን ሪፎርም ከሚያስፈጽሙ አካላት ብቻ ማግኘት ወይም ከእነሱ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም ሀገርንና ሕዝብን በዘላቂነት ተጠቃሚ ለማድረግ በዚህ ረገድ መንግሥት የሚወስዳቸውንም ሕግ የማስከበር ርምጃዎች ዜጎች በሚችሉት ሁሉ ሊደግፉት ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ጊዜ እናመሰግናለን።**

**አቶ በረከት፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ለኢንቨስትመንት ተጨማሪ አቅም የሚሆነው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያ

**አንተነህ ቸሬ**

የመጀመሪያው ምዕራፍ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር (Home-Grown Economic Reform Program) ብዙ የፖሊሲ ሃሳቦችን በውስጡ ያካተተና መጠነ ሰፊ የኢኮኖሚ ዓላማዎችንና ግቦችን ያሳካ እንደነበር መንግሥት ሰሞኑን አስታውሶ፣ ሁለተኛው ምዕራፍ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር ደግሞ ቀሪ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ እንደሚያስችል ገልጿል።

የመንግሥትን ኢንቨስትመንት ውጤታማነት በማሻሻል በዓለም አቀፍ ደረጃ ዘመናዊና ተወዳዳሪ የኢኮኖሚ ሥርዓትን መገንባት በመርሃ ግብሩ ትግበራ ከተቀመጡ ግቦች መካከል አንዱ ሆኖ ይጠቀሳል። በሌላ በኩል ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሩ ከተገነባባቸው አራት ዋና ዋና ምሰሶዎች መካከል አንዱ፣ ፈጠራን የሚያበረታታ ምቹ የኢንቨስትመንትና የንግድ ዘርፍ ከባቢና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ነው።

ኢትዮጵያ ሰሞኑን ወደተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር ትግበራ ገብታለች። ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሩ ዋና ዋና የፖሊሲ ርምጃዎችና የሚጠበቁ ሀገራዊ ፋይዳዎች መካከል አንዱ፣ በገበያ ላይ የተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት (Floating Exchange Rate) ትግበራ ነው። ሀገሪቱ ወደተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር ትግበራ መግባቷ መገለፁን ተከትሎ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት መሻሻሉን ይፋ አድርጓል። በዚህም የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት በገበያ ላይ ወደተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት ተሸጋግሯል።

ይህ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች መካከል አንዱ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ እንደሆነ መንግሥት ገልጿል። አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት የውጭ ምንዛሬ ግኝትንና ክምችትን ሊጨምሩ የሚችሉ ልዩ ልዩ አሠራሮችን አስተዋውቋል። ሥርዓቱ የውጭ ምንዛሪን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስተላለፍ ግዴታን በመተው ላኪዎችና ንግድ ባንኮች ያፈሩትን የውጭ ምንዛሪ ለራሳቸው ማስቀረት የሚያስችላቸው በመሆኑ፣ ለግሉ ዘርፍ የሚሰጠው የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት በእጅጉ እንዲሻሻል ያደርጋል።

በአዲሱ አሠራር በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች ከውጭ የሚላክላቸውን ሐዋላ፣ በውጭ ምንዛሪ የሚከፈል ደሞዝን/የኪራይ ገቢን እና ሌሎች ገቢዎችን የሚያስቀምጡባቸውን የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች እንዲከፍቱ፣ እንዲሁም እነዚህን የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች ተጠቅመው የውጭ አገልግሎት ክፍያዎችን እንዲፈጽሙ ተፈቅዷል። መመዘኛውን የሚያሟሉ የውጭ ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ (Ethiopian Securities Exchange) እንዲሳተፉ ተፈቅዷል። በልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ የሚሠሩ ኩባንያዎች የውጭ ምንዛሪ ገቢያቸውን ሙሉ በሙሉ ለራሳቸው መያዝን ጨምሮ ልዩ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም መብት ተሰጥቷቸዋል።

ምርቶችን ወደ ውጭ የሚልኩ ነጋዴዎች ካፈሩት የውጭ ምንዛሪ ገቢ ለራሳቸው ያስቀሩት የነበረው 40 በመቶ ወደ 50 በመቶ ከፍ ብሏል። ቀደም ሲል ባንኮች ለተለያዩ ገቢ ሸቀጦች የሚጠቀሙበት የውጭ ምንዛሪ አሠራርና አደላደል ደንቦች ቀሪ ሆነዋል። ከዚህ በተጨማሪም አሁን በሥራ ላይ ካሉና በባንኮች ከተቋቋሙ የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች (ForEx Bureaus) በተጨማሪ ባንክ ያልሆኑ የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች (Independent ForEx Bureaus) ይቋቋማሉ፤ ለእነዚህ ባንክ ላልሆኑ የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎችም በገበያ ዋጋ የውጭ ምንዛሪ ጥሬ ገንዘብ እንዲገዙና እንዲሸጡ የሥራ ፈቃድ ይሰጣቸዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምህረቱ ስለውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያው በሰጡት ማብራሪያ፣ ማሻሻያው ለኢንቨስትመንት እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ገልፀዋል። አቶ ማሞ እንዳስረዱት፣ የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የውጭ ኢንቨስተሮችን በመሳብ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በማሳደግ፣ የሀገሪቱን የንግድ ሥርዓት ከአጎራባችና ከአቻ ሀገራት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

‹‹በአሁኑ ወቅት፣ ኢትዮጵያ ከታላላቅ የአፍሪካ ኢኮኖሚዎችና በማደግ ላይ ከሚገኙ በርካታ ሀገራት መካከል የውጭ ምንዛሪ ቁጥጥር ሥርዓትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ያለባት ሀገር ናት። ሀገሪቱ ከሕዝብ ብዛት፣ ከሠለጠነ የሰው ኃይል፣ ከተመጣጣኝና ከተወዳዳሪ ግብዓቶች (የሰው ጉልበት፣ መሬት)፣ ከተጠናከረ የአየር ትራንስፖርትና ከተሻሻለ ሎጂስቲክስ፣ ከኃይል አቅርቦት፣ ከተፈጥሮ ሀብትና ከማዕድናት አኳያ በብዙ መልኩ ለኢንቨስትመንት ምቹና ሳቢ ብትሆንም፣ እነዚህ ሁሉ ዕድሎች በአስቸጋሪና ጥብቅ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ምክንያት ውጤታማነታቸው የተጠበቀውን ያህል አልሆነም። » ብለዋል። ስለዚህ፣ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት ለውጭ ኢንቨስተሮች ማነቆ ሆኖ የቆየውን አሠራር ለማስወገድና ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እንደሚጠቅም አመልክተዋል።

አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን ያበረታታል፤ የማምረት ሥራቸውን እንዲያስፋፉና የገበያ ድርሻቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል። በኢንዱስትሪና በፍጆታ ዕቃዎች ምርት ዘርፎች የተሠማሩ ተኪ ኢንዱስትሪዎች፣ በተለይም በአሁኑ ወቅት ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› በተሰኘው ንቅናቄ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ በርካታ ኢንዱስትሪዎች ከማሻሻያው ተጠቃሚ ይሆናሉ።

እሳቸው እንደተናገሩት፣ የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የግሉን ዘርፍ ለማሳደግና የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማዘመን እንዲሁም ኢኮኖሚውን ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ለማድረግ የተወሰዱ ሌሎች በርካታ የማሻሻያ ርምጃዎችን የሚደግፍና የሚያጠናክር ይሆናል። ከእነዚህም የማሻሻያ ርምጃዎች መካከል፣ ቀደም ሲል ለግል ዘርፍ/ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ የነበሩ ዘርፎችን (ለምሳሌ ቴሌኮም፣ ሎጂስቲክስ፣ ባንክ፣ ካፒታል ገበያ፣ ጅምላና ችርቻሮ ንግድ) ክፍት ማድረግ፣ የንግድ ማሳለጫ ሥርዓት ማሻሻል፣ የግል ዘርፍና በመንግሥት ፕሮጀክቶች በአጋርነት ማሳተፍ፣ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ማቋቋም ... ይገኙባቸዋል። በእነዚህ ዘርፎች የተደረጉ ለውጦች ለግሉ ዘርፍና ለኢኮኖሚ ዕድገት አያሌ መልካም ዕድሎችን ቢከፍቱም፣ የውጭ ምንዛሪ ፖሊሲዎች ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች ማነቆ ሆነው በመገኘታቸው ማስተካከያ ማድረግ የግድ እንደሆነም ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ፣ የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና ሌሎች የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ የወጡ በርካታ የለውጥ ርምጃዎችን ለማጠናከር እንደሚረዳ አቶ ማሞ ምህረቱ አስረድተዋል።

የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለሀገሪቱ ኢንቨስትመንት እድገት ማነቆ ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል። በአዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ይፋ የተደረጉት አሠራሮች በኢንቨስትመንት ሥራ ውስጥ ቁልፍ ሚና ካላቸው ግብዓቶች መካከል አንዱ ለሆነው የውጭ ምንዛሬ ግኝትና ክምችት መጨመር ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ ተብሎ ይጠበቃል።

በፕላንና ልማት ሚኒስቴር የልማት እቅድና የመንግሥት ኢንቨስትመንት አስተዳደር የሥራ ክፍል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ በረከት ፍስሃጽዮን የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያው ለኢንቨስትመንት ማደግ በጎ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይገልፃሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፣ ቀደም ሲል የነበረው አሠራር ኢኮኖሚውን አንቆ የያዘ የውጭ ምንዛሪ አሠራር ሥርዓት ነበር። አዲሱ አሠራር ይህንን በመሻገር ውጤታማ የሆኑና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን የሚቻልባቸውን ዘርፎች ተደራሽ ለማድረግ ያስችላል። ይህም ለሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ይሆናል።

> **የውጭ ምንዛሪ እጥረት** ለሀገሪቱ ኢንቨስትመንት እድገት ማነቆ ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በአዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ይፋ የተደጉት አሠራሮች በኢንቨስትመንት ሥራ ውስጥ ቁልፍ ሚና ካላቸው ግብዓቶች መካከል አንዱ ለሆነው የውጭ ምንዛሬ ግኝትና ክምችት መጨመር ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ ተብሎ ይጠበቃል

የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ውጤቶችን በግብዓትነት የሚጠቀሙ አምራቾች ይኖራሉ። ሀገራዊ አቅምን በአግባቡ በመጠቀም የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት ሂደትን የሚያበረታታም ይሆናል።

የውጭ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ያበረታታል። የውጭ ኢንቨስተሮች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ ይዘዋቸው የሚመጡ እድሎችና መልካም አጋጣሚዎች እንዳሉ መታወቅ አለበት። በሪፎርሙ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ የሚደረግ ከፍተኛ መጠን ያለው ፋይናንስ ይኖራል። በአጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያው ኢንቨስትመንቱን ያነቃቃዋል። ማሻሻያው የመንግሥትን ገቢ በማሳደግና የመንግሥት ወጭ አስተዳደርን በማዘመን የማኅበራዊና የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች እንዲጠናከሩ ያግዛል።

‹‹ማሻሻያው የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን የማሳደግ አቅም ይኖረዋል። በሀገር ውስጥ አቅም ሊመረቱ የሚችሉ ምርቶችን የማምረት እድል በመስጠት፣ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ሰፊ እድል ይከፍታል፤ በዚህም ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል ይፈጠራል። ትክክለኛውን ዋጋ ይዞ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን በማረጋገጥ የተመጣጠነ የወጪና የገቢ ንግድ እንዲኖር ያደርጋል። ተወዳዳሪ መሆን መቻል ደግሞ የማክሮ ኢኮኖሚ ስብራቶችን ለመጠገን ይረዳል። ይህም የንግድ ሚዛን ጉድለትንና የክፍያ ሚዛንን ለማስተካከል ትልቁን ድርሻ ይወስዳል። በዚህም የተረጋጋ ኢኮኖሚ ይፈጠራል። በግሉ ዘርፍ ላይ የተመሠረተ ጠንካራ ነጻ ኢኮኖሚ ዋናው ማረጋገጫው በገበያ የተመሠረተ ዋጋ መኖሩ ነው›› በማለት ያብራራሉ።

ቀደም ሲል የነበሩ የማክሮ-ኢኮኖሚ መዛባቶችን ለማረም እና ኢኮኖሚው ያጋጠሙትን መዋቅራዊ ችግሮች ለመፍታት መጠነ ሰፊ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ሲደረጉ እንደነበር የሚያስታውሱት አቶ በረከት፣ አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያም የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሩ አካል እንደሆነ ይገልፃሉ።

አቶ በረከት እንደሚያስረዱት፣ የውጪ ምንዛሪ አስተዳደርን የተመለከተው ጉዳይ የኢኮኖሚውን ዋነኛ ማነቆዎችን ለመፍታት መከናወን የነበረበት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ አካል ነበር። በመጀመሪያው ምዕራፍ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባትን ለማረም፣ የእዳ ጫናን ለማቃለል፣ የሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለማሳደግ እና የኢኮኖሚ እድገት ምንጮችን ለማስፋት በተከናወኑ ሥራዎች ብዙ ውጤቶች ተገኝተዋል።

የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያው በሁለተኛው ምዕራፍ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር የሚተገበር ነው። ‹‹በአጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በድንገት የተከሰተ ሳይሆን ቀደም ሲል ሲተገበሩ ከነበሩት ጋር የሚያያዝና በሁለተኛው ምዕራፍ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር ሊተገበር እቅድ የተያዘለት ነው›› በማለት ያስረዳሉ።

የፐብሊክ ፖሊሲ ጥናት ባለሙያው ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ በበኩላቸው፣ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያው ለሀገሪቱ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ብሎም ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ትልቅ እምርታን የሚያስገኝ ርምጃ እንደሆነ ይናገራሉ ‹‹ይህን ዓይነቱን አሠራር ካደጉት ሀገራት በተጨማሪ ብዙ የአፍሪካ ሀገራትም ይጠቀሙበታል። የውጭ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ያበረታታል። ከካፒታል ገበያው መጀመር እና ከውጭ ባንኮች መግባት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ኢንቨስተሮች ሊመጡ ይችላሉ። ይህ ደግሞ በሀገሪቱ ኢንቨስትመንት እንዲጨምር ያደርጋል። ማሻሻያው ኢኮኖሚውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊጠቀምበት በሚችለው መንገድ ሊያራምደው ይችላል›› ይላሉ።

ማሻሻያው ውጤታማ እንዲሆን መንግሥት የኮንትሮባንድ ስራዎችን፣ በተለይም ከሀገር ውስጥ የሚወጣውን ገንዘብ መቆጣጠር እንዲሁም ሰላምና መረጋጋትን ማስፈን እንዳለበትም ይመክራሉ።

# ስግብግብ ነጋዴዎቻችን ልብ የሚገዙት መቼ ይሆን ?

**እስማኤል አረቦ**

የኑሮ ወድነቱ አንዱ የታዳጊ ሀገራት ፈተና ነው። ኢትዮጵያም የዚሁ ችግር ሰለባ ነች። ከወር እስከ ወር ከዓመት እስከ ዓመት በየጊዜው ማሻቀቡና ተባብሶ መቀጠሉን የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት በየጊዜው የሚያወጣቸው መረጃዎችና በማኅበረሰቡ ላይ የሚታየው የኑሮ ጫና ያመላክታል። በየጊዜው እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ወድነት አሁን ላይ በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የማኅበረሰብ ክፍል በእጅጉ እየፈተነ ይገኛል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች እንደሚሉት፣ የኑሮ ወድነት ተከሠተ የሚባለው የማኅበረሰቡ የመግዛት አቅም ወይም ገቢ ማነስ ከዋጋ ግሽበት ጋር ተደምሮ የሚፈጥረው የመግዛት አቅም ሲዳከም ነው። በኢትዮጵያ ከመሠረታዊ የምግብ ፍጆታዎች እስከ ሌሎች ቁሳቁሶች ድረስ የዋጋ ግሽበቱ በየጊዜው እያሻቀበ ቢሆንም፣ የአብዛኛው የማኅበረሰቡ ክፍል ገቢ ወይም የመግዛት አቅም ግን ከዋጋ ግሽበቱ እኩል ማደግ አለመቻሉን የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ።

ለዋጋ ግሽበት ዋነኛ ምክንያቶች ከሚባሉት መካከል የአቅርቦት እና ፍላጎት አለመመጣጠን፣ የገበያ ምኅዳር ብልሽት ወይም ሕገ ወጥ ደላሎች በገበያ ውስጥ የሚፈጥሩት ጣልቃ ገብነት እና የጥሬ ገንዘብ ሥርጭት መብዛት በቀዳሚነት የሚነሱ መሆናቸውን የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። በኢትዮጵያ እየታየ ላለው የዋጋ ግሽበት ዋና ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው የምግብ ነክ ሸቀጦች፣ በተለይ የእህል ዋጋ መናር ነው።

ለዋጋ ግሽበቱ መባባስ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም እንደ ሀገር ፈተና እየሆኑ ካሉ ችግሮች አንዱ ስግብግብ ነጋዴዎች በአቋራጭ ለማትረፍ የሚያደርጉት ሩጫ ነው። ሰሞኑን መንግሥት ይፋ ያደረገውን የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያን ተከትሎ ከዶላር መጨመር ጋር ተያይዞ በመርካቶና በሌሎች ዋና ዋና የገበያ ስፍራዎች የሸቀጦችን ዋጋ ለማናርና በአቋራጭ ለመበልጸግ እየተደረጉ ያሉ ሩጫዎች ማሳያዎች ናቸው።

ይህንኑ ተከትሎ ያለ አግባብ የዋጋ ጭማሪ ባደረጉ፤ ምርትን በደበቁና ባከማቹ በአጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥርዓቱን ተከትሎ የተደረገውን የዶላር ዋጋ ማሻሻያ ምክንያት በማድረግ በአቋራጭ ለመክበር ጥረት ባደረጉ 9 ነጋዴዎች ላይ ርምጃ መውሰዱን አዲስ አበባ ንግድ ቢሮ አስታውቋል።

የንግድ ቢሮው እየወሰደ ያለው ርምጃ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ቢሆንም ድርጊቱ ግን አስተዛዛቢ ነው። መንግሥት የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርም ማድረጉን ባስታወቀበት በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ሸቀጦችን በመደበቅ፤ በማከማቸትና ከልካቸው በላይ ዋጋ በመቆለል የሸቀጦች ዋጋ እንዲንር እና ኑሮ ውድነቱ እንዲባባስ ለማድረግ ሲሞክሩ ታይተዋል። እነዚህ ስግብግብ ነጋዴዎች ምንም ሰብዓዊ ርህራሄ የሌላቸው ከመሆናቸውም በላይ ከራሳቸው ሆድና የንዋይ ጥማት ውጭ ለሀገርም ሆነ ለወገን የሚጨነቅ ህሊና እንደሌላቸው በገሃድ ታይቷል።

ሀገር የሚጸናው በዜጎች ባለቤትነትና ተሳትፎ ነው። ስለሀገራቸው የሚቆረቆሩ ዜጎች ባሉበትና በማንኛውም ጉዳይ ላይ በባለቤትነት የሚሳተፉ ዜጎች በበዙበት ሀገር ላይ ልማት ይስፋፋል፤ ሰላም ይሰፍናል፤ ብልጽግና ያብባል። በተቃራኒው ስግብግቦች በበዙ ቁጥር ሀገር ሕገ ወጥነት ይስፋፋል፤ ወንጀል ይበራከታል። ማህበራዊ ቀውስ ይሰፍናል። ስለዚህም ስግብግቦችን ማጋለጥና ማውገዝ እንዲሁም ለሕግ አሳልፎ መስጠት የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት መሆን አለበት።

ማንኛውም ወንጀልና ሕገ ወጥ ድርጊት ከሕዝብ የተሰወረ አይደለም። ሕዝብ የማይሰማው፤ ሕዝብ የማያየው ሁኔታና ድርጊት የለም። ለዚህም ነው ሕዝብ ያመነበትና የተሳተፈበት ነገር ሁሉ ውጤት የሚያመጣው። በተለይም ሕዝብና መንግሥት እጅና ጓንት ሆነው የተሳተፉባቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ ውጤት ማምጣታቸው፤ ፍሬ ማፍራታቸው አይቀርም።

በተለይም በአሁኑ ወቅት የኑሮ ውድነቱን ከተገቢው በላይ የሚያጦዙና ከህብረተሰቡ ችግር ማትረፍ የሚፈልጉ ስግብግብ ነጋዴዎችን በማጋለጥና ለሕግ እንዲቀርቡ ማድረግ የሚቻለው ሕዝብ ሲተባበር ብቻ ነው። በህብረተሰቡ ላይ የኑሮ ጫና እየፈጠሩ የሚገኙ ሕገ ወጥ ነጋዴዎች በሰዓታት ልዩነት የሸቀጦች ዋጋ እንዲንር በማድረግ ህብረተሰቡን ለምሬት መዳረጋቸው የዕለት ተዕለት ተግባራቸው ቢሆንም የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ከሕዝብ ዓይን ሊያመልጡ አይችሉም። ስለሆነም ለእነዚህ ስግብግቦች ጊዜ መስጠት የበለጠ ዋጋ ያስከፍላልና ሕዝቡ ነቅቶ ሊጠብቃቸው ይገባል።

ሕገወጦች ነፍስ የሚዘሩት ምንቸገረኝነት ሲሰፍን ነው። ሀገር የዜጎች ናትና ሕገወጥነትን አይቶ እንዳለየ ማለፍ ዜግነትን አሳልፎ መስጠትና ሕገወጥነት እንዲስፋፋ ማድረግ መፍቀድ መሆኑም መረዳት ይገባል። በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት ኃላፊዎችም ቢሆኑ ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚመጡ ጥቆማዎችን ዋጋ በመስጠት አጥፊዎች ተገቢውን ፍትህ እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል።

በአጠቃላይ በምንቸገረኝነት የሚታለፉና የመንግሥት ኃላፊነት ብቻ ተደርገው የሚወሰዱ ውሳኔዎች በመጨረሻ የሚጎዱት ሕዝብ ነው። ስለዚህም ሕዝቡ በይገባኛል ስሜት በመንቀሳቀስ የሚታዩ ሕገወጥ ተግባራትንና ብልሹ አሰራሮችን ሊታገልና መስመር ሊያሲዛቸው ይገባል።

መንግሥት ይፋ ያደረገው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥርዓት ሀገሪቱ ለገባችበት የኢኮኖሚ አጣብቂኝ ሁነኛ መፍትሔ ይዞ እንደሚመጣ እሙን ቢሆንም ከወዲሁ ማሻሻያውን ለራሳቸው ጥቅም ለማዋል የሚሯሯጡ ስግብግብ ነጋዴዎችን አደብ ማሳያዝ ግን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በእነዚህ ነጋዴዎች የተነሳ ህብረተሰቡ የበለጠ በኑሮ ውድነቱ ወገቡ መጉበጥ የለበትም።

የእነዚህ ነጋዴዎች ስግብግብነት ታክሎበት የዋጋ ግሽበት አሁንም ትልቁ የሀገሪቱ ፈተና ነው። አሁን ያለው የዋጋ ንረት አምናና ካቻምና ከነበረበት የ33 በመቶ ደረጃ ወደ 23ነጥብ 3 በመቶ ዝቅ ቢልም አሁንም የኑሮ ውድነቱን በማባባስ ረገድ ፈተና ሆኖ ዘልቋል። በተለይም የምግብ ዋጋ ንረት 27 በመቶ መሆኑ ችግሩ ዝቅተኛውን የህብረተሰብ ክፍል የሚጎዳ ነው።

ይህንን ችግር ለመቀነስ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር ጥረት መደረጉ፤ የገንዘብ ዝውውሩን ለመቀነስ የገንዘብ እና ፊሲካል ፖሊሲ በጥብቅ መተግበሩና ነዳጅን በመሳሰሉ ቀጥተኛ የኑሮ ውድነትን በሚያስከትሉ ሸቀጦች ላይ ድጎማ መደረጉ የኑሮ ውድነቱ አሁን ካለበት እንዳይጨምር አስተዋጽኦ ያደረጉ ቢሆንም ካለው የህብረተሰባችን የመግዛት አቅም አንጻር በቀጣይ በርካታ ጥረቶችን በማድረግ የዋጋ ግሽበቱ ከተቻለ እንዲቀንስ ካልሆነ ባለበት እንዲቆም ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይም በንግድ ሥርዓቱ ላይ ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁንም የሚተዳደረው በግብርና ነው። ኢትዮጵያም ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገራት በሚታረስ የእርሻ መሬትና በግብርና ምርት ቀዳሚ ሀገር ናት። ሆኖም በተቃራኒው የግብርና ምርቶችና ሌሎች መሰረታዊ አቅርቦቶች እጥረት ካለባቸውና ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ከሚታይባቸው ሀገራትም አንዷ ናት። በአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣምና በተለያዩ ብልሹ አሰራሮች ምክንያት በየቀኑ እየጨመረ የሚሄደውም የሸቀጦች ዋጋ መናር በዜጋው ላይ ከፍተኛ የኑሮ ውድነትን በመፍጠር ሕዝቡን ለምሬት እየዳረገው ነው።

በተለይም ህብረተሰቡ በዕለት ተዕለት በሚጠቀምባቸው መሠረታዊ ፍጆታዎች ላይ እየታየ ያለው የዋጋ ንረት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዜጎችን ሕይወት እጅግ እየተፈታተነው ይገኛል። በእህል፣ በጥራጥሬ፤ በአትክልት ምርቶች፤ በግንባታ ዕቃዎች እና በቤት ኪራይ ላይ የዋጋ ጭማሪው አሳሳቢ ሆኗል። ነገሩን ይበልጥ ከባድ የሚያደርገው ደግሞ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት እየተመዘገበ ያለው የምግብ ነክ ሸቀጦች ላይ መሆኑ ነው። ትራንስፖርት፣ የትምህርት ቤት ክፍያና የመሳሰሉት ሲጨመሩበት የሕዝቡን ኑሮ ችግሩን ከድጡ ወደ ማጡ እያደረገው ነው።

> **እነዚህ ስግብግብ ነጋዴዎች ምንም ሰብዓዊ ርህራሄ የሌላቸው ከመሆናቸውም በላይ ከራሳቸው ሆድና የንዋይ ጥማት ውጭ ለሀገርም ሆነ ለወገን የሚጨነቅ ህሊና እንደሌላቸው በገሃድ ታይቷል**

በየቀኑና በየሰዓቱ የሚጨምረው የሸቀጦች ዋጋ በተለይም ዝቅተኛው የህብረተሰብ ክፍል ኑሮ እንደምርጊት እንዲከብደው ምክንያት ሆኗል። መሸቶ በነጋ ቁጥር «ከገበያ ጠፍተዋል» ፤ «ዋጋ ጨምሯል» የሚሉት አገላለጾች ህብረተሰቡን በሰቆቃ ውስጥ እንዲኖር እያደረጉት ነው። ለዚህ ደግሞ የስግብግብ ነጋዴዎች አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

በአሁኑ ወቅት የዋጋ ግሽበቱ 23 በመቶ አካባቢ ነው። በአሃዝ የተቀመጠው የዋጋ ግሽበት ከፍተኛ ከመሆኑ አንፃር የዋጋ ግሽበቱ ምክንያት ምንድነው ብሎ በደንብ አይቶ መፍትሔ መስጠቱ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ነው። የኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት ባለሁለት አሃዝ ነው። በሠለጠነው ዓለም የዋጋ ግሽበት ከሁለት በመቶ ብዙም የዘለለ አይደለም። በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ደግሞ ከአራት እስከ ስድስት በመቶ እንዳይበልጥ ጥረት ይደረጋል። ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያም በርካታ ሥራዎች እንደሚቀሩ አመላካች ነው።

ለሀገሪቱ የዋጋ ግሽበት የምርት እጥረት ብቻ የሚፈጥረው አይደለም። የዘመናዊ ግብይት ዕጦት እና የደላሎችና ሕገወጥ ነጋዴዎች መበራከት ለችግሩ መባባስ መንስዔ ናቸው። የኢትዮጵያ ገበያ 200 እና 300 በመቶ ትርፍ የሚያዝበት ነው። ይህ በዓለም ላይ የለም። ይኼ አካሄድም በፖሊሲ ጭምር ታግዞ ሊስተካከል ይገባል።

የሀገሪቷ ገበያ ሥርዓት ዘመናዊ ባለመሆኑ የፖሊሲ ለውጥ ያስፈልገዋል። ሰሞኑን መንግሥት ወደ ትግበራ ያስገባው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥርዓትም ለዚህ ሁነኛ መፍትሔ ይዞ ይመጣል ተብሎ ይጠበቃል። በሀገራችን ውስብስብና ኋላ ቀር የሆነ፣ የገበያ ሥርጭት ነው ያለው። አንዳንድ ቦታ እንዲያውም በሞኖፖል የተያዘ ይመስላል። በተለይ ሸቀጣ ሸቀጥ ላይ ገበያው በሞኖፖል ተይዟል። ስለዚህ ይህንን በመፍታት አዳዲስ ኩባንያዎችን በማስገባት የውድድር ሜዳውን በማስፋት ረገድ ትልቅ ዕድል እንደሚፈጥር ታምኖበታል። ዘርፉን ለሚቀላቀሉ የሀገር ውስጥና የውጭ አዳዲስ ኩባንያዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ድጋፍ ከተደረገ በአንድ ቀን አዳር ዋጋ የተጋነነ ዋጋ በመጨመር ራሳቸውን ሚሊየነር ለማድረግ የሚጥሩት ስግብግብ ነጋዴዎች ከእንግዲህ ወዲያ ቦታ አይኖራቸውም።

ይህ አካሄድም በውድድር ዋጋ የሚቀንስበትን መንገድ በመፍጠር የኑሮ ውድነቱ እንዲረጋጋ ያደርጋል። ቀልጣፋ የሆነ አቅርቦትና ውድድር ከተፈጠረ የዋጋ ግሽበቱን መቀነስ ይቻላል። አዲሱ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያም ሁሉም ነገር በገበያ እንዲወሰን በር ስለከፈተ በጥቂት ነጋዴዎች ተይዘው የቆዩ ዘርፎችም በርካታ ተዋናዮች እንዲኖሩ በማድረግ ሸማቹ በርካታ አማራጮች እንዲኖሩት ያስችላል።

ግሽበቱን ለመቀነስ በቂ ምርት ሊኖር ይገባል ከተባለ ደግሞ ሸማቾች የሚጠቀሙባቸው ከሀገር ውስጥ ሆነ ከውጭ የሚገኝ ምርት በበቂ ሁኔታ እንዲቀርብ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትን ከፍ ማድረግ። ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ላይ ግሽበቱ የሚታይ ከሆነ በቂ ምርት እንዳይኖር የውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ሊሆን ይችላልና በቂ የውጭ ምንዛሪ በማቅረብ እያስተካከሉ መሄድ። አሁን ያለው አሠራር እየፈጠረ ያለው የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ የሚቀረፀው ፖሊሲ የውጭ ኩባንያዎችንም በማስገባት እንዲረጋጋ ማድረግንም ይጠይቃል። የውጭ ምንዛሬ ማሻሻያ ሥርዓቱም ለዚህ ምቹ ምህዳር ይፈጥራል።

# የዘመን ጥበብ

# ከካሜራ በስተጀርባ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ከካሜራ በስተጀርባ ብዙ ጉዳዮች ሆድና ጀርባ ናቸው ከቴሌቪዥን መስኮት ውስጥ እንደ ፊት መስታየት የምንመለከታቸው ምስሎች ወደ ገሀዱ ዓለም ሲመጡ ግን ያንኑ መሳይ እውነተኛ ምስል አያስመለክቱንም የመስታየቱን አቅጣጫ እየዘወሩ ሲያስመለክቱን የነበሩ ሰዎችን ምስል ከእውነተኛው የሕይወት መስታየታቸው ላይ ከተመለከትነው ምናልባትም አራንባና ቆቦ ሊሆንም ይችላል የጠላነውን ወደን የምንወደውንም አምርረን እንጠላው ይሆናል የሚያበግኑን ቀዝቀዝ እንዳለ ውሃ የሚያረሰርሱን ሆነው ይገኛሉ

ከካሜራው ፊት ከነበረው ይኼው መስታየት ውስጥ ጨካኝ የመሰሉ ከካሜራው በስተጀርባ የርህራሄን ጥግ ሊያሳዩን ይችላሉ ሲያስቁን የነበሩ በራሳቸው ሕይወት ግን ሊያስለቅሱን እንደሚችሉ አይተናል ከካሜራው ፊት ለጋሽና መጽዋች የነበሩት ከገሀዱ ቀማኝ ዘራፊዎች ሆነው ብንመለከት አይግረመን በኑሯቸውና ባላቸው ነገር ቀንተን ምነው እነርሱን ባደረገኝ ያልናቸው ሰዎችን ምናልባትም መልሰን ከእነርሱስ ሰውረኝ የምንላቸው ይሆናሉ ከካሜራው በስተጀርባ የምንመለከተው አንዳንድ እውነታ አንዳንዴም ሰቅጣጭ ነው እንደ እሬት ይመራል የምንጠብቀው እንዳልጠበቅነው፣ የምናውቀውም እንደማናውቀው ሆኖ የማናይበት ምክንያት የለም

ከካሜራ በስተጀርባ የምናደርገው ይኼው ምልከታችን የተቃና ይሆን ዘንድ ለማሳያነትም ስለ አንድ ፊልም እናነሳለን ፊልሙ በራሱም "ከካሜራ ጀርባ "ይሰኛል የፊልም ብቻም ሳይሆን የሕይወት ተዋንያንም እንዳሉ ይነግረናል


እነማን ከካሜራ በስተጀርባ?...እውነተኛ የጥበብ ልጆች፣ ቤተኞች፣ ልማደኞችና ለምደኞች ይገኙበታል በበጎች መሀል የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎችም አድፍጠውበታል ራሳቸውን ጎድተው የጥበብን አጥንት ከሚያለመልሙት ጎን ለጎን ቆመው ጥበብን እስከ አጥንቷ ድረስ እየቀረጠፉ የሚግጧት አልጠፉም ከካሜራው በስተጀርባ ያለው ትልቁ ውጋትም ገንዘብ ነው የጥበብ ካዝናዋ በገንዘብ የተራቆተ በመሆኑ ይህን ተከትሎ ደራሽ አልባሽ መስለው ከውጭ የሚገቡ የጥበብ አንበጦች ሞልተዋል እንደ አጠቃላይ ከካሜራው ጀርባ የፊልምና ድራማ ተዋንያንን፣ ደራሲና ዳይሬክተሮችን፣ አዘጋጅ ፕሮዲዩሰሮችን፣ ሙዚቀኛ ድምጻውያንን፣ የሚዲያ ጋዜጠኞችና የማኅበራዊ ሚዲያ ዘዋሪዎችን እናገኛለን እንዲሁም ደግሞ በየዘርፉ ውስጥ በየስርቻው የተሸጎጡትን ደላሎችንም አናጣም

ተባርከው ለጥበብ የቆሙ፣ እንደ እርግማን መዥገር ተጣብቀው የሚመጠምጡትንም እናይ ይሆናል እነርሱ እስካሉ ድረስ ብቃትና ብቁነት ሁሌም ቦታ አለው ማለት ከንቱ እምነት፣ የባዶ ጣሳ ጩኸት ነው ተክሎች እየተረገጡ አረሞች ተኮትኩተው ሊንዠረገጉ ይችላሉ እውነታዎች ተደፍጥጠው ቅጥፈቶች ሊያብቡና ፍሬ የሚሰጡ መስለው ሊታዩም ይችላሉ

በሁሉም የጥበብ ዘርፎች ውስጥ የተጠናከረ ኢንዱስትሪ ባለመኖሩ ለተራቡ ጅቦች መና መስሎ ቢታይ አይደንቅም ጥቂት ቡድኖችና ግለሰቦች በሀብት ላይ ሀብት፣ በዝና ላይ ዝና የሚታጠቁበት ዓለም ከካሜራው በስተጀርባ እንደተጎለተ ነው በዚህ ምክንያትም ለፍቶ አዳሪዎች ጾም አዳሪ ናቸው በሥራቸው እንደፊኛ ተወጥረው በቀለማት ሲንሳፈፉ የምናውቃቸው በኑሯቸው ግን የተነፈሰ ፊኛ መስለው ይታያሉ ስማቸው እንደ ጎልያድ ገዝፎ ሕይወታቸው ግን እንደ ዳዊት ጠጠር በተአምር ነው ዋንጫና ሰርተፍኬቱ ክምር ጓዳና ኪስ ግን ቁር ይሆናል ሁልጊዜም ባይሆን አዘጋጁ በሽልማት ዝግጅቶች አመሃኝቶ የራሱን ኪስ በመሙላት፣ ለሠራውና ለተሸላሚው ግን ጠብ የሚል ነገር ሳያደርግ በስሙ ሲነግድበት መኖር አለ

ጥበብና የጥበብ ሰው ለሽቀጥ ገበያ አውጥተው በካሜራ ካስገመቱና ካስጎበኙ በኋላ "በሉ ደህና ሰንብቱ!" ይባላሉ የካሜራው ጀርባ እንጂ የካሜራው ፊት ይህን አይነግረንም ሁሌም አሳምሮና አስጊጦ ሲደልለን ይኖራል

"ከካሜራ ጀርባ" ፊልም...የዚህ ፊልም ደራሲና ዳይሬክተር ኤሊያስ ወርቅነህ ሲሆን፤ ጥር 8 ቀን 2015 ዓ.ም ተመርቆ ለእይታ በቅቷል ከዚህ ቀደም በፊልሞችም ይሁን በድራማዎች ውስጥ ከካሜራ ፊት ያለውን የራሳችንና የማኅበረሰባችንን ሕይወት በአርቲስቶቹ ውስጥ ስንመለከት ቆይተናል በዚህ ፊልም ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ከካሜራ በስተጀርባ ያለውን የራሳቸውን ሕይወት አሳይተውናል ፊልሙም በይዘትና በዓይነቱ የመጀመሪያው ነው ለማለት እንችላለን




ከካሜራ በስተጀርባ ያሉትን የፊልም ዳይሬክተሮችን ሰቆቃና እንግልት የሚያስመለክተን ሞገስ በተሰኘው ገጸ ባህሪ ውስጥ ነው ይህ ገጸ ባህሪም የአብዛኛዎቹን የፊልም ደራሲና ዳይሬክተሮችን መልክ ተላብሶና ይዞ ሲጓዝ እንመለከታለን ሞገስ በፊልሙ ዘርፍ ዕውቅና አዋቂ ከመሆኑም በሠራቸው ሥራዎቹ በርካታ ዕውቅናና ሽልማቶችን ያገኘም ነው እጅግ ዝነኛና ሁሉም አብሮት ለመሥራት የሚፈልገው ዓይነት ሆኖ ይታያል በአሥር ፊልሞቹ የዓመቱ ምርጥ በመባልም በተለያዩ ጊዜያቶች አሸናፊ ለመሆን የበቃም ደራሲና ዳይሬክተር ነው ይህን ያህል ጊዜ እያሸነፈና እየተሸለመ የኖረው ሞገስ ግን በራሱ ፊልም ለመሥራት ቀርቶ ኑሮውን ለመምራት የሚሆነው ቤሳ ቤስቲን የለውም ፊልሙ ሲጀምር ገና ሞገስ አሸናፊ የሆነበትን የመድረክ አጀብ እያሳየን ይጀምራል ቀጥሎም የሽልማት ዋንጫውን በእጁ እንደታቀፈ አስፋልቱን በእግሩ እየደቃ ለብቻው ጥግ ጥጉን ይዞ እንደቆዘመ በእግር ወደ ቤቱ ሲመለስና ተጋፍቶ የታክሲ ወረፋ ሲጠብቅም ይገኛል

ለሚሠራው አዲስ ፊልም ፕሮዲዩስ የሚያደርገውን ፍለጋ የማይጠናው የባለሀብት ደጅ የለም አንዳንዶቹም ይስማሙና የወደዱትን ገጸ ባህሪ "እኔ የምጫወተው ከሆነ... እገሊትን እገሌን..." የሚል ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጡለታል ይወጣና ይሄዳል አብዛኛዎቹም ሀገራዊና ታሪካዊ ጭብጥ የያዘውን ፊልም ኮሜዲ አድርገህ የምትሠራው ከሆነ ብቻ ይሉታል አሁንም ጥሏቸው ይሄዳል ከብዙ ፍዳና አሳር መልስም ፕሮድዩስ የሚያደርገውን ያገኛል ነገር ግን ልፋትና ውጣውረዱን የምትመለከተው እህቱ ግን ለጉዳይ ያስቀመጠችውን 4 መቶ ሺህ ብር ሥራበትና ትመልሳለህ በማለት ትሰጠዋለች የፊልም ሥራው ከተጀመረ በኋላም በከባድ ህመም ሲሰቃይ የሚኖረው የእህቱ ልጅ ሁኔታ ጭንቀት ሲዘራበት እንመለከታለን ከዚያ በፊት በሠራው በአንደኛው ፊልሙ ውስጥ ያሠራትን አንዲት ሴትንም በአጋጣሚም መንገድ ያገኛታል እርሱ ባሠራት ፊልም ምክንያት የውጭ ሀገር ዕድል አግኝታ፣ ሀብትም አካብታ ባለጠጋ ለመሆን የበቃች ነበረች ከተመለሰች በኋላም ላደረገላት ውለታ ለፊልም ሥራው የሚረዳውን ዘመናዊ ካሜራ ብትልክለትም አበሳው ከጉምሩክ ደጃፍ ጠበቀው ከመንግሥት አካላት በየጊዜው የተሰጡትን ሰርተፍኬቶች በቦርሳው አጭቆ ቢሄድም ካሜራው የተገዛበትን አንድ ሦስተኛ ያህል ዋጋ ቀረጥ እንዲከፍል ተገደደ ለመክፈል ያቅተውናም ካሜራው ወደመጣበት እንዲመለስ ይደረጋል

"የጥበብ ቤርሙዳ..."ከካሜራ በስተጀርባ" ሌላ አንድ አስቀያሚ የሕይወት ዐሻራ ከነመዳፉ ያስመለክተናል ሴትነትን ተላኮ፣ ውበት ላይ አድፍጦ እንደ እሽኮኮ ሹክክ! እያለ ይቀርባል ይጠጋል እንደ እባብ በደረቱ እየተሳበ ደርሶ ይናደፋል የሳር ውስጥ እባብ ሳያዩት ሳያስተውሉት ምራቁን እየደፈቀ ተጠቅልሎ ጭን ውስጥ ይሸጎጣል ሴትነትን ያራክሳል ውበትን ያጠለሻል ገንዘብ ዓይን አስጨፍኖ ህሊናን ይደፍናል በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የእሳት ረመጡ የሚንተከተክበት የነውር መጋረጃ ተሰቅሏል ዝነኛም ይሁኑ ጀማሪ፣ በካሜራ ውስጥ ያለፉ ቆንጆ አርቲስቶችን በተመለከቱ ቁጥር እንደ ሸቀጥ በገንዘብ ገዝተው፣ ከቀናቸው የእርድ በሬ ያደርጓቸዋል በየሙዚቃው ክሊፕ ውስጥ የሚሠሩ ሞዴሎች፣ የፊልም ተዋንያን፣ ድምጻውያን፤ በአጠቃላይ በኪነ ጥበቡ አካባቢ በሚሠሩ ዕውቅ የጥበብ ባለሙያ ሴቶች ላይ ያንዣበበው ጭልፊት አሞራ የዋዛ አይደለም

በዚህ ፊልም ደራሲው እውነታውን በፊልሙ ውስጥ ሲያሰፍር፣ ራሱ ዳይሬክተሩም መርቶ ገሀዱን ሲገልጥ ከጉያቸው ስር ከሚሆነው በመነሳት ነው በፊልሙ ውስጥ አብረው በአንድ ቤት ውስጥ ከሚኖሩት ከአራት ሴት ገጸ ባህሪ መካከል ሁለቱ የፊልም ተዋንያን ናቸው አንዷ ሴት የሙዚቃ ክሊፖች ላይ የምትሠራ ሞዴል ስትሆን፤ ሌላኛዋ ደግሞ በማስታወቂያው ዘርፍ ላይ የምትሠራ ሆና ትገኛለች

ከካሜራ ፊት ብዙኃኑ የሚያውቃቸው ቆነጃጂት የጥበብ ባለሙያ ናቸው ከካሜራ በስተጀርባ ግን ለማመን የሚከብድ አስቀያሚና ወልጋዳ ሕይወት የሚኖሩ ሆነው ይገኛሉ የሚፈልጉት ዝናን ብቻ አይደለም ገንዘብ ትልቁ የሕይወት መርህ ቁልፋቸው ነው ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ደግሞ በባለገንዘቡ እቅፍ ውስጥ ይወድቃሉ ቆነጃጅቱን እና ባለሀብቱን የሚያገናኘው መስመር ደግሞ ጥቁር የንስር ዓይን በያዙ ደላሎች ይታጠራል ደላላውም አማራጩን በምግብ ሜኑ መልክ ያቀርብለታል ፈላጊውም የሴቶቹን ሁኔታ ከነፎቶ የያዘውን ባህረመዝገብ እያገላበጠ፣ የፊቷን ውበት እየመዘነ፣ የጭንና ዳሌዋን ወርድና ስፋት እየለካ "ለዛሬው ይህቺ ትሁንልኝ" ይላል

ለቆነጃጂቱም ቀድሞውኑ መስመሩ ላይ ያሉበት ከሆነ የሎተሪ ዕጣ የወጣላቸው ያህል ነው ከባለሀብት ባለሀብት፣ ከገንዘብ ገንዘብ፣ ከሀገር ሀገር እያማረጡ ዓለማቸውን መቅጨት ብቻ ቆንጆና ያማረ ቅንጡ መኪና ይዞ ሀገር ምድሩን እንቁልልጭ ማለት ብቻ ምናልባትም የባለሀብቱና የደላላው ፈተና የሚበዛው አዳዲስ ብቅ በሚሉና ገና ባልተቀጠፉ ትኩስ አበባዎች ነው ምክንያቱም ለእርዱ ቢታጬም እነርሱ ግን የመጡት ለጥበብና ለሙያው ፍቅር ነውና "ወግድ ዞር በል!" ማለታቸው አይቀርም

በፊልሙ ውስጥ የቡድኑ አምስተኛ አባል ሆና የምትመጣዋ ሴት የአንደኛዋ የልጅነት ጓደኛ ናት ከልጅነቷም ጀምሮ ተዋናይ የመሆን ልዩ ፍላጎትና ምኞት አላት ከክፍለ ሀገር ሆና ከቤተሰብ ጎረቤቱ ጋር ተሰባስበው ጓደኛዋ የተወነችባቸውን ፊልሞች በተመለከቱና ቃለ መጠይቆቿን በተከታተለች ቁጥር ሁሉ እየደወለች "እባክሽን እኔም ወደ ትወናው የምገባበትን መንገድ አመቻቺልኝ" በማለት ትማጸናታለች የትወና ፍቅሯንና ህልሟን፣ በዝነኛዋ ጓደኛ ከካሜራ ፊት ከቴሌቪዥን መስኮት ውስጥ የምትመለከተውን የሚያስቀና ሕይወት እንጂ ከካሜራ በስተጀርባ ስላለው የጉድ ዓለም የምታውቀው አንድም ነገር የለም ውስጠ ሚስጥሩን የምታወቀው ዝነኛዋ ጓደኛዋም የእርሷ ዕጣ ፈንታ እንዳይደርስባት ስትል ለብዙ ጊዜያት "እንደምታስቢው ቀላል አይደለምና ይቅርብሽ" ስትልና ጥያቄዋን ስትገፋባት ኖራለች ገፍታ ስትመጣባት ግን ጥያቄዋን ተቀብላ መንገዶችን ለማመቻቸት እንደምትሞክርላት በመግለጽ ቃል ትገባላታለች

ልጅትም ጓዟን ጠቅልላ ከክፍለ ሀገር አዲስ አበባ ትመጣለች በደባልነት ከሚኖሩት የቆነጃጅት ማኅበርም ተቀላቅላ ነገረ ሥራዎቻቸውን ሁሉ ትመለከትና በልቧም ትታዘባቸው ነበር ከባሕል ወግና ሥርዓት ያፈነገጡ ድርጊቶቻቸውን እየተመለከተች ደስ የማይሉ ስሜቶች ያጭሩባት ነበር ገና በመጀመሪያዎቹ ቀናትም ለብሳ የመጣችውን ቀያይረው የእነርሱን አለበሷት ባይመቻትም ሙደገዳዳ ላለመባል የእነርሱንም ተጫማች የሀር መሳይ ባለ ቆንዳላ ጸጉሯን ዘመናዊ መልክ አበጃጁለት ከሁሉም ነገሮቻቸው እያሸተቱ ይዘዋት ወደ ጭፈራ ቤት አቀኑ

ድሮም ውብ ልጃገረድ ነበረችና ከዚያ ጭፈራ ቤት ውስጥ የተመለከታት ቅንዝረኛ ሁሉ ዓይኖቹን ሰዶ በስሜት እረመጥ ይቃጠል ጀመረ ገና በመጀመሪያው ዕለትም አዲሶቹን ጓደኞቿን ጠጋ ብሎ ለሽያጭ እንዲያቀርቡለት ይጎተጉታቸውም ገባ እያመቻቹና እያመቻመቹ ግድ የለህም አታስብ በማለት በዚያው የመጀመሪያ ዕለት ከልጅነት ጓደኛዋ ጋር ወደ ቤት የሸኛቸው ሀብታም "እንቺ ለጸጉርሽ መሠሪያ" በማለት የታሠረውን ረብጣ ብር ያወጣል አይሆንም ብትልም ጓደኛዋ "ያዢ ለጸጉርሽ ነው ምን ታካብጂያለሽ" በማለት ብሩ እንዳያመልጥ ከሰውየው ተቀብላ በእጇ ታሲዛታለች ገና በቀናት ውስጥም ያቺ ጨዋ ልጅ አመል ጀማመራት ልክ እንደ እነርሱው እየሆነች መጥታ እነርሱንም አስናቀች ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሯ ሄደች ክንፍ አውጥታም በረረች ክንፏ ተሰብሮም ወድቃ ተሰበረች

በኪነጥበብ ሥራዎች ውስጥ በፍጹም...ፍጹምነት አይኖርም "ከካሜራ ጀርባ "ፊልም ውስጥ ደራሲው አንድ አዲስ ነገርን ለማስመለከት የሄደበትን መንገድ አለማድነቅ አይቻልም ጥሩ ነገሮቹ እንዳሉ ሆነው፤ ነገር ግን እንደ ባለሙያ ሳይሆን እንደ አንድ ተመልካች የታየኝን ክፍተት ለማንሳት እወዳለሁ ርዕሱ ሰፊና ግዙፍ እንደመሆኑ ከካሜራ ጀርባ ያለውን ሁሉንም እውነታዎች አጭቆ በአንድ ፊልም ውስጥ ለማስቀመጥ የማይቻል እንደመሆኑ እይታውን ለሁሉም እውነታዎች አማካኝ በሆነ መንገድ ከማስቀመጥ አንጻር ይጎድለዋል

ሁሉንም ባለሙያዎች ከማማከል ይልቅ በሁለት የታሪክ ጽንፎች ላይ የሚጓዝ ዓይነት ነው በዋናነት የሚታዩት ጀርባዎች በደራሲና ዳይሬክተሮች ስቃይ እና ውበታቸውን በመጠቀም ያለቦታቸው ገብተው በሚፈታፈቱ ቆነጃጂት ሴቶች ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ ሚዛናዊ የሆነውን የበስተጀርባ እውነታ ለማግኘት ፈታኝ ያደርገዋል የገጸ ባህሪያቱ የማንነት ስሮች የተንሳፈፈ ነገር ይታይባቸዋል ከመነሻው ጀምሮ በአንድ መሠረት ላይ ከሚጓዝ የታሪክ ፍሰት ይልቅ ቅንጭብጭብ ያሉ ትዕይንቶች በዛ ብለው የሚታዩበት በመሆኑ ብዙ ነገሮች ግልጽ እንዳይሆኑ ያደርገዋል እኚህ ሁሉ እያሉም ግን ፊልሙ እጅግ ውብና ድንቅ ነው

ከፊልሙ መጨረሻ...ፊልሙ ተሠርቶ ተጠናቀቀ በተመረቀ ዕለትም ከውጭ ሀገር የመጡ የፊልም ባለሙያዎች ተመልክተው ወደዱለት ለአንድ የውጭ የፊልም ፌስቲቫልም ፊልሙ ተመረጠ ያ የእህቱ ትንሽ ልጅም በድንገት ይታመምና ወደ ውጭ ሀገር ወስዶ ለማሳከም ሲል ፊልሙን ለሚገዙ በርካሽ ያቀርብላቸዋል በዚህ መሀልም ፊልሙ ተሰርቆ ዩቲዩብ ላይ ተጭኗል የሚል መርዶ ይሰማል የነበራትን ገንዘብ ሁሉ ለፊልም ሥራው የሰጠችውን የእህቱን ልጅ ለማዳን ሲል በየጎዳናው ሁሉ ሳይቀር መለመን ይጀምራል "ይኼ ደራሲና ዳይሬክተሩ ሞገስ አይደል...ምን ሆኖ ነው?፣ ያው ገንዘቡን በሱስ ጨርሶት ይሆናል..." እያሉ የሚያፌዙበትም ነበሩ በመጨረሻም ቀደም ሲል ካሜራ ልካለት ከነበረችው ደግ ሴት 1 ሚሊዮን ብር ይደርሰዋል ወዲያውኑ ሲሮጥ እያለከለከ እህቱ ቤት ደጅ ላይ ከመድረሱ የለቅሶና የዋይታ ጩኸት ይሰማል አምርሮ እያለቀሰም ከመሬቱ ላይ ይወድቃል ይህ ሁሉ ጉድና መአትም ከካሜራው ጀርባ ያለ ነው

ጥበብ መከራና መዘዟ ብዙ ነው የሚወዳት እየተረገጠ የሚጠላት ሊሾምባት ይችላል ገፊዎች እየተንደላቀቁ ጥበበኞችን ሲያረግፉ መኖርም አለ በኛ ሀገር የጥበብ ኢንዱስትሪ ውስጥ በብዛት የምንመለከተው ከደረሰው ፍሬ እየቀጠፉ የሚበሉት ሥራውን የሠሩት ልፋተኞቹ ሳይሆኑ ከዳር ቆመው የሚያሠሩት ናቸው "በጨው ደንደስ በርበሬ ትወደስ" እንዲሉ የሠራው ፈጦ ያልሠራው ይጨበጨብለታል አንዱ በሌላው ጫንቃ ላይ ቆሞ ምስጋናና ሀብት፣ ዝናና በረከት ያጋብሳል የሠራው ከሥራው በልቶ ሊጠግብ ሲገባው የበይ ተመልካች ሆኖ እያሸተተው ብቻ ዕድሉን ወይ ሙያውን ሲራገም ይኖራል

"ከካሜራ ጀርባ" በፊልሙ ውስጥ የአንድ የፊልም ዳይሬክተር ሆኖ የሚጫወተው ሞገስ የተሰኘው ገጸ ባህሪ እንዲህ ዓይነቶቹ ነገሮች ተስፋ አስቆርጠውት ቢያጣ ወደ አረብ ሀገር ለመሰደድ የወሰነባቸው ጊዜያት ብዙ ነበሩ ጥበብ ግን ለስቃይ ጣር ሁን ብላ አሁንም እየጎተተች ገፍታ ወደመሀል ታስገባዋለች ብዙ የጥበብ ሰዎች "ጥበብ የማይለቅ ዛር አለባት" ሲሉ ግነት ወይም ውሸት አይደለም ይኼው ዛር ባይኖርማ የካሜራን ጀርባ ተመልክቶ በቤቷ የሚቀመጥ ማንስ ይኖር ነበር? አብዛኛውን ጥበበኛ ጠልፋና ጠላልፋ የምታስቀምጠው በዚሁ ዛሯ ነው።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ሴቶች እንደ አልማዝ እንዲያበሩ

አስናቀ ፀጋዬ

እየሩሳሌም ሙሉዘውድ የአስራ ሰባት ዓመት ታዳጊ ናት። በዘንድሮው ዓመት የአስራ ሁለተኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ወስዳለች። እናቷ ናቸው ገና የስድስተኛ ክፍል ተማሪ እያለች ‹‹ላይፍ ሴንተር›› ወደተሰኘው ወላጅ አልባ ህፃናትና መበለቶች መርጃ ድርጅት ያመጧት። እናቷ ወደዚህ ድርጅት ያመጧት ከባለቤታቸው ጋር በመለያየታቸው ብቻቸውን ማሳደግ ስላልቻሉ ነበር።

እየሩሳሌም ወደ ላይፍ ሴንተር ከመጣች ወዲህ በርካታ አገልግሎቶችን በነፃ ማግኘት ችላለች። ትምህርቷን በሚገባ እየተከታተለችም ነው። ለትምህርቷ አጋዥ የሆኑ መፅሃፍቶችን ከድርጅቱ ታገኛለች። ቤተ መፃህፍት እንደልቧ ትጠቀማለች። በየዓመቱ የትምህርት መሣሪያዎች ድጋፍ ይደረግላታል። በመምህራን የጥናት አገልግሎት ታገኛለች። ዓመታዊ የተማሪዎች የመዝናኛና የጉዞ ፕሮግራሞች ላይም ትገኛለች።

ከዚህ ባለፈ እየሩሳሌም ድርጅቱ በየጊዜው በሚያዘጋጃቸው የልጃገረዶች የሕይወት ልምድና ማይንድ ሴት ሥልጠናዎች ላይ ትሳተፋለች። በተለይ በአፍላ የእድሜ ክልል ውስጥ እንዴት አመዛዝኖ ውሳኔዎችን ማሳለፍ እንደሚቻል በቅርቡ ከወሰደችው ሥልጠና መገንዘብ ችላለች። በሕይወት ውስጥ ፈተናዎችን እንዴት ተቋቁሞ ማለፍ እንደሚቻልም ነው ከዚህ ሥልጠና የተረዳችው። በቀጣይም ጥሩ ውጤት አምጥታ ዩኒቨርሲቲ እንደምትገባም ተስፋ ሰንቃለች።

ወይዘሮ ሙሉ ግርማይ የላይፍ ሴንተር ኢትዮጵያ መስራችና ዋና ሥራ አስፈፃሚ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፣ ድርጅቱ ያዘጋጀው ሥልጠና እድሜያቸው ከአስራ አምስት ዓመት በላይ ለሆኑ ልጃገረዶች ነው። ሥልጠናውን ለማዘጋጀት የተፈለገውም በዚህ እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሴቶች በርካታ ውጣውረዶችን ስለሚያልፉና በሴትነታቸው የሚገጥሟቸውን ልዩ ልዩ ችግሮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ለዚያም ነው ድርጅቱ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ለሴቶች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ የሚገኘው። ሴቶች በየእድሜ ደረጃቸው ማወቅ የሚገባቸውን ነገር እያወቁ እንዲሄዱ፣ በሳልና ትክክለኛ ውሳኔ እንዲወስኑ ለማድረግም ነው ሥልጠናዎችን በየጊዜው የሚያመቻቸው።




እስካሁን በተሰጠው ሥልጠና ሴቶቹ በብዙ መልኩ ተቀይረዋል። ነገር ግን ሥልጠና ብቻውን በቂ አይደለም። ሥልጠናው ተከታታይና ወቅታዊ መሆን ይጠበቅበታል። የአሁኑ ሥልጠና መሪ ቃልም ‹‹shine out›› የሚል ነው። ይህ መሪ ቃል የተመረጠበት ምክንያት ሴቶች እንደሴቶች የሚያልፉባቸው በርካታ ችግሮች ስላለ ነው። ነገር ግን ሴቶች ችግር እንደ አልማዝ እንዲያጠነክራቸው፣ ተደብቀው እንዳይቀሩ፣ እንዳይጎዱ፣ ህብረተሰቡ እንዳይደብቃቸው፣ አጉል ባህል ወደኋላ እንዳያስቀራቸውና ተሸንፈው እንዳይቀሩ ነው የሚፈለገው።

ከአፈር ወጥተው መሰናክሎች ሳያቆሟቸው እንደ አልማዝ እንዲያበሩ፣ ህብረተሰቡን እንዲጠቅሙ፣ ለራሳቸው እንዲቆሙ፣ ጠንካራ ሴቶች እንዲሆኑ አሁን የተዘጋጀው ሥልጠና ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ልጃገረዶች ቢዳረስ መልካም ነው። ለጊዜው ግን ላይፍ ሴንተር የሚረዳቸው ሴቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሠራል።

ወይዘሮ ሙሉ እንደሚናገሩት፣ ሥልጠናው ዋናው ዓላማ ልጃገረዶች በአእምሮና በአስተሳሰብ እንዲያድጉ ለማስቻል ነው። ሴቶች በሕይወት የሚያልፉባቸው መሰናክሎች እንደመኖራቸው፣ በእኩል የማይታዩ እንደመሆናቸውና ካሉባቸው በርካታ ተፅእኖዎች አንፃር ጠቃሚ ዜጋዎች እንዲሆኑና ጠንካራ ሆነው እንዲወጡ ማስቻል የሥልጠናው ዓላማ ነው። አዕምሯቸውን የማሳደግ፣ ውሳኔያቸውን እንዲያስተካክሉ ለማድረግም ነው ሥልጠናው የተዘጋጀው።

ልጃገረዶች በዚህ እድሜያቸው መሰናክሎች ሳያስቀሯቸው ለራሳቸው እንደ አልማዝ በርተው ሌሎች አቻዎቻቸውም ምሳሌ እንዲሆኑ ነው የሚፈለገው። ሴቶቹ ወድቀው እንዲቀሩና ከትምህርት ቤት እንዲያቋርጡ አይፈለግም። የማያስፈልግ ግንኙነት ውስጥ ገብተው ከሕይወታቸው ወደ ኋላ እንዲቀሩ አያስፈልግም። ስለዚህ መጠንከር አለባቸው። ይህ ደግሞ የሚመጣው በሥልጠና ነው።

በዚህ ሥልጠና 50 ልጃገረዶች ተሳትፈዋል። ልጃገረዶቹ በሕይወታቸው እንዲያውቁ፣ እንዲማሩና እንዲበስሉ ስለሚፈለግ ከዚህ ሥልጠና በኋላ ውሳኔያቸው ጤናማ እንዲሆን ነው የሚጠበቀው። አልባሌ ቦታ ላይና ጥፋት ላይ እንዳይገኙ፣ ለሀገር ሸክም እንዳይሆኑ፣ ተምረው ሀገራቸውን የሚጠቅሙ ጀግናና መሪ ሴቶች እንዲሆኑ ነው የሚፈለገው። ይህ በአንድ ጊዜ የሚመጣ ባይሆንም ቀስ በቀስ ግን ይህንን እንዲሆኑ ነው የሚፈለገው።

ፓስተር ጆይ ሜጋኒዝ ደግሞ ተቀማጭነቱን በአሜሪካን ሀገር ያደረገው የሆራይዘን ኢንተርናሽናል በጎ አድራጎት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ናቸው። ድርጅታቸው ወላጅ አልባ ህፃናት ላይ የሚሠራ ሲሆን ከላይፍ ሴንተር ኢትዮጵያ ጋር በትብብር ይሠራል። ላለፉት አስር ዓመታትም ከላይፍ ሴንተር ጋር ሲሠራ ቆይቷል። በዚሁ ትብብር መሠረትም ነው ለልጃገረዶች ሥልጠና ለመስጠት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው።

ልጃገረዶች በየቀኑ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ተቋቁመው በጨለማ ውስጥ እንዲያንፀባርቁ ነው የሕይወት ልምድ ሥልጠና የተሰጣቸው። ከዚህ በፊትም ተመሳሳይ ሥልጠናዎች ሰጥቷል። የሥልጠናው ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ሴቶች ችግሮችን ተቋቁመው እንዴት ወደ ስኬት መውጣት እንደሚችሉ ነው። በአካል፣ በአዕምሮና በመንፈስ የጠንራና ጤናማ ሕይወት እንዲኖሩ የሚያስችል ነው። በሥልጠናውም ሴቶች የተለያዩ የሕይወት ልምዶችንና የበሰሉ ውሳኔ ሰጪነትን ተምረዋል። ሴቶች ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ ድርጅቱ ከላይፍ ሴንተር ጋር ሆኖ እገዛ እያደረገ ይገኛል። ወደፊትም ይህን እገዛ አጠናክሮ ይቀጥላል።

# ዓለም አቀፍ



## የአሜሪካ ብሔራዊ ዕዳ መጠን ከ35 ትሪሊዮን ዶላር አለፈ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የአሜሪካ ብሔራዊ ዕዳ መጠን ከ35 ትሪሊዮን ዶላር አለፈ፡፡

የዓለማችን ልዕለ ሃያል ሀገር አሜሪካ የዕዳ መጠኗ ከ35 ትሪሊዮን ማለፉን የሀገሪቱ ግምጃ ቤት በድረገጹ አስታውቋል።

የሀገሪቱ የእዳ መጠን በአሜሪካ ታሪክ ከፍተኛው እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን የዋጋ ግሽበት መፈጠሩ፣ ለዩክሬን እና እስራኤል የተሰጠው ርዳታ በየጊዜው መጨመር እና የፊታችን ሕዳር ወር ለይ የሚደረገው ምርጫ መንግሥት የሚበደረውን የገንዘብ መጠን እንዲጨምር አድርጓል ተብሏል።

የአሜሪካ መንግሥት እዳ መጠን ባሳለፍነው ጥር ላይ 34 ትሪሊዮን ደርሶ የነበረ ሲሆን ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ አንድ ትሪሊዮን ዶላር ተጨማሪ ብድር መበደሩ ተገልጿል።

አሜሪካ ያለባት ብድር ከጠቅላላ ዓመታዊ ምርቷ በላይ ነው የተባለ ሲሆን ብድሩ ከዓመታዊ እድገቱ ጋር ሲነጻጸር 120 በመቶ ደርሷል ተብሏል፡፡

የሀገሪቱ ብድር መጠን በዚሁ ከቀጠለ በ2054 የአሜሪካ ጠቅላላ ብድር ከዓመታዊ እድገቱ ጋር ሲነጻጸር 166 በመቶ ያህል እንደሚጨምር ተገልጿል፡፡

የብድር መጠን መጨመሩን ተከትሎ በርካታ አሜሪካውያን ፖለቲከኞች እና ነጋዴዎች ተቃውሟቸውን የገለጹ ሲሆን ጉዳዩ መፍትሔ እንደሚያሻው በመናገር ላይ ናቸው፡፡

አሁን ላይ የአሜሪካ መንግሥት በየቀኑ አምስት ቢሊዮን ዶላር እየተበደረ ነው የተባለ ሲሆን ቢሊየነሩ ኢለን መስክ ይህ እብደት ነው ሲል በኤክስ አካውንቱ ላይ ጽፏል፡፡

## የሱዳን መንግሥት ከፈጥኖ ደራሽ ሃይሉ ጋር ለመደራደር ተስማማ

በጋዜጣው ሪፖርተር



የሱዳን መንግሥት በአሜሪካ መንግሥት በቀረበው የድርድር ጥያቄ መሠረት ከፈጥኖ ደራሽ ሃይሉ ጋር ለመደራደር ተስማምቷል።

በአሜሪካ እና ሳኡዲ አረቢያ መሪነት በሲውዘርላንድ ጄኔቫ እንዲካሄድ ለቀረበው የድርድር ጥሪ የሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መንግሥት ፈቃደኛ መሆኑን አስታውቋል።

አሜሪካ የሱዳን ጦር እና የፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች ጦር በፈረንጆቹ ነሐሴ 14 በስዊዘርላንድ የተኩስ አቁም ንግግር እንዲሳተፉ ጥሪ ማቅረቧን ተከትሎ፤ የፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች መሪ መሀመድ ሀምዳን ደጋሎ “በሀገሪቱ ወጥ የሆነ የተኩስ አቁም እንዲደረግ እና የሠብዓዊ ርዳታ ለተቸገሩ ሁሉ እንዲደርስ” በንግግሩ ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆናቸውን ወዲያው ማሳወቃቸው ይታወሳል።

በግብጽ፣ በጂቡቲ፣ በኬንያ፣ በሳኡዲ አረቢያ እና በሌሎች አካላት ሁለቱን ተፋላሚዎች ለማደራደር የተደረገው ሙከራ ውጤታማ ሳይሆን ዘልቋል።

የሀገሪቱ ጦር በሀገር ከጂነት ከፈረጀው የፈጥኖ ደራሽ ሃይል ጋር ለመደራደር ፈቃደኝነት አላሳየም። የጄኔቫው ጉባዔ ሁለቱን አካላት በአንድ ክፍል ውስጥ ለማገናኘት ለወራት ከተሞከሩ ሙከራዎች ቀዳሚው ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

የሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከትናንት በስቲያ ማምሻውን ባወጣው መግለጫ ከፈጥኖ ደራሽ ሃይሉ ጋር ለመደራደር ፈቃደኛ ነኝ ቢልም፤ ሀምዳን ዳጋሎ የሚመሩት ጦር ከተቆጣጠራቸው ስፍራዎች እንዲለቅ እና ሌሎች አካባቢዎችን ለመቆጣጠር የሚያደርገውን ውግያ እንዲያቆም ቅድመ ሁኔታ አስቀምጧል።

በተጨማሪም በድርድሩ አጀንዳዎች ዙርያ ከአሜሪካ ባለሥልጣናት ጋር መነጋገር እንደሚፈልግ ገልጿል።

ሮይተርስ እንደዘገበው ሱዳን ካሏት 18 ክልሎች ስምንቱን መቆጣጠር የቻለው የፈጥኖ ደራሽ ሃይሉ የሀገሪቱ ጦር ያቀረበውን ቅድመ ሁኔታ የመቀበል እድሉ ዝቅተኛ ቢሆንም ሁለቱም ወገኖች ለመደራደር ያሳዩት ፈቃደኝነት አንድ ርምጃ ነው ብሏል።

በጄኔቫ የሚካሄደው ድርድር በአሜሪካ እና ሳኡዲ መሪነት የሚደረግ ሲሆን የአፍሪካ ህብረት፣ ግብጽ እና የተባበሩት አረብ ኤሜሬትስ በታዛቢነት እንደሚታደሙ ተገልጿል።

15 ወራትን ያስቆጠረው ጦርነት 10 ሚሊዮን ገደማ ሰዎች እንዲፈናቀሉ እና 10 ሺህ ሰዎች እንዲገደሉ ምክንያት ሆኗል።

በተጨማሪም ብሔርን መሠረት ያደረጉ ግድያዎች የተስፋፉ ሲሆን በተለይም የፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች ጦር በምዕራብ ዳርፉር የብሔር ጥቃት ፈጽሟል የሚል ክስ ይቀርብበታል።

አሜሪካ በቅርቡ የሱዳን ተፋላሚ ኃይሎች የጦር ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ድሜዳሜ ላይ መድረሷን ማሳወቋ ይታወሳል።

# ስፖርት

# ተራማጁ ኢትዮጵያዊ ኦሊምፒያን

ዓስማየሁ ግዛው

ኢትዮጵያ በዘመናት የደመቀ የኦሊምፒክ መድረክ ውጤታማ የአትሌቲክስ ታሪክ ገናና ስም ያተረፈችው በረጅም ርቀትና በማራቶን ውድድሮች ነው:: ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ በመካከለኛ ርቀቶችም ውጤታማ መሆን ችላለች:: የአትሌቲክሱ አንድ አካል በሆነው የእርምጃ ውድድሮች ግን እንኳን የውጤት እምብዛም የተሳትፎ ታሪክ የላትም:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ ባህል እየተቀየረ መጥተል:: በኦሊምፒክ መድረክ ባይሆንም በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ የተለያዩ ቻምፒዮናዎች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም በእርምጃ ውድድሮች ከተሳትፎ ባሻገር ውጤት ማስመዝገብም እየቻሉ ነው::

ለዚህ ትልቁ ማሳያም 2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ የአትሌቲክስ ውድድሮች ዛሬ ሲጀመሩ የመላው አፍሪካ ጨዋታዎች የእርምጃ ቻምፒዮኑ አትሌት ምስጋና ዋቁማ በ20 ኪሎ ሜትር ኢትዮጵያን በብቸኝነት ወክሎ የሚፎካከር ተራማጅ ኦሊምፒያን መሆኑ ነው::

መንፈሰ ጠንካራው አትሌት ምስጋና ዋቁማ በብዙ የሕይወት ውጣ ውረዶች አልፎ ዛሬ ጠዋት 2፥30 ላይ በሚጀመረው የፓሪስ ኦሊምፒክ የ20 ኪሎ ሜትር የእርምጃ ውድድር ለመጀመሪያ ጊዜ ታሪካዊ ተሳትፎውን ያደርጋል::

ኢትዮጵያዊው ተራማጅ ኦሊምፒያን እዚህ ደረጃ ለመድረስ ብዙ ዋጋ ከፍሏል:: ከሆቴል አስተናጋጅነት እስከ ጽዳትና የጉልበት ሠራተኝነት ሕይወት ውስጥ አልፏል:: ለሚገጥሙት የሕይወት ፈተናዎች ሽብረክ ሳይል በጠንካራ ሥራና በሰነቀው ትልቅ ህልም ግን ዛሬ በዓለም ትልቁ የስፖርት መድረክ ሀገሩን ወክሎ ለመፎካከር በቅቷል::


በኦሮሚያ ክልል ወንጪ የተወለደው አትሌት ምስጋና እንደ በርካቶቹ ኢትዮጵያውያን ኦሊምፒያኖች በግብርና ሥራ ከሚተዳደር ቤተሰብ ነው የተገኘው:: ቴክኖሎጂ ብዙም ካልተስፋፋበትና በቀላሉ መረጃዎችን መግኘት ከማይቻልበት ስፍራ ተነስቶ እዚህ መድረሱ ጥንካሬውን አጉልቶ ያሳየ ነው:: በተወለደበት አካባቢና በትምህርት ቤት ሩጫ በመሞከር ወደ ስፖርቱ የገባው አትሌት በጊዜው ትኩረት ሰጥቶ የሚመለከተው አልነበረም:: ከትውልድ ሥፍራው ወደ አዲስ አበባ ሲያቀና የልጅነት የሩጫ ፍቅሩ አልተለየውም:: አዲስ አበባ መጥቶ ግን ከስፖርትና ሥራ ጎን ለጎን ማስኬድ ከብዶት ያቋረጠውን ትምህርቱን ከሁለት ዓመት በኋላ ጀምሮ ከልምምዱ ጋር በማጣጣም አሁን የ11ኛ ክፍል ትምህርቱን እየተከታተለ በኦሊምፒክ ይወዳደራል::

አትሌቱ የእርምጃ ተወዳዳሪ ከመሆኑ በፊት በ10 እና 5ሺ ሜትር የሩጫ ውድድሮች ሲሳተፍ የቆየ ቢሆንም በአንድ እንስት አሠልጣኝ ምክር የእርምጃ ተወዳዳሪነቱን አሃዱ ብሎ እንደጀመረ በተለያዩ አጋጣሚዎች ባደረጋቸው ቃለምልልሶች ተናግሯል:: የእርምጃን ስፖርት ቴክኒክ ያስተማረችውም ይችው መካሪው አሠልጣኙ ነበረች:: ያምሆኖ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ብዙም ደፍረው ሲገቡበት በማይታየው የእርምጃ ስፖርት በክለብ ለመታቀፍ ነገሮች ቀላል አልነበሩም:: ከፌዴራል ማረሚያ ክለብ ጋር ለስምንት ወራት ያክል ልምምዱን ቢሠራም የመቀጠር እድሉን ማግኘት አልቻለም ነበር:: በዚህም ተስፋ ሳይቆርጥና ሌላ አማራጭ በመፈለግ፣ ባገኘው አጋጣሚ በአዲስ አበባ ክለቦች ቻምፒዮና ኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ወክሎ በመወዳደር በሶስተኛነት በማጠናቀቁ በክለቡ የመታቀፍ እድል አገኘ::

አትሌት ምስጋና ክለብ ካገኘ በኋላ በ20 ኪሎ ሜትር የእርምጃ ውድድር በሀገርና አህጉር አቀፍ ውድድሮች ስኬታማነቱን ደጋግሞ አስመስክሯል:: በአህጉር አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያን ወክሎ መሳተፍ የጀመረውም ንግድ ባክን በተቀላቀለ የመጀመሪያ ዓመቱ ሲሆን፣ ብቃቱን በማሳደግ ውጤታማ አትሌት ሆኗል::

ኢትዮጵያን ወክሎ የመጀመርያ አህጉር አቀፍ ተሳትፎውን ባደረገበት የ2022ቱ የሞሪሺስ ሴንት ፒየሪ የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና አራተኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቋል:: በካሜሮን ያውንዴ በተካሄደው የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና እና በጋና አክራ በተካሄደው 13ኛው የመላው አፍሪካ ጨዋታዎች የወርቅ ሜዳሊያዎችን ማጥለቅ ችሏል:: እአአ በ2023 የአፍሪካ ከ20 ዓመት በታች ቻምፒዮና በ 10 ሺ ሜትር የእርምጃ ውድድር የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊም ሆኗል:: በወቅቱ ባስመዘገባቸው ድሎች በ20 ኪሎ ሜትር እርምጃ ከዓለም 76 ደረጃን መያዝም ችሎ ነበር:: ከወራት በፊት በቱርክ አንታላይ በተካሄዳው የዓለም 20 ኪሎ ሜትር እርምጃ ውድድርም 10ኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቋል::

በአንታላይ በተካሄደው የዓለም እርምጃ ቻምፒዮና 1 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ከ51 ሴኮንድ ውድድሩን ያጠናቀቀ ቢሆንም ከውድድሩ ውጪ በሆነ አትሌት ተተክቶ ለፓሪስ ኦሊምፒክ ተሳትፎ መብቃት ችሏል:: ኢትዮጵያ 15ኛ የኦሊምፒክ ተሳትፎዋን የምታደርግበት 33ኛ የፓሪስ ኦሊምፒክ ለዚህ አትሌት ሌላ የተለየ ደማቅ ታሪክ ነው::







አትሌት ምስጋና ዋቁማ በፓሪስ ኦሊምፒክ 20 ኪሎ ሜትር የእርምጃ ውድድሩን ዛሬ ያደርጋል